# የአባቶች አለቃ አብርሃም

እንደገና ኦሪት ዘፍጥረት፡ 22ኛው ምዕራፍ፡ ከ15ኛው ቁጥር ጀምሮ አንብበን፡ አገልግሎታችንን በመጀመር ለጥቂት ደቂቃዎች ብቻ ለመናገር እንጠብቃለን። ዘፍጥረት 22፡ ከ15ኛው ቁጥር ጀምሮ እናንብብ።

**የእግዚአብሔር መልአክም አብርሃምን ከሰማይ ሁለተኛ ጊዜ ጠራው፡**

**እንዲህም አለ፡ እግዚአብሔር በራሴ ማልሁ ይላል፡ ይህን ነገር አድርገሃልና፡ አንድ ልጅህንም፡ አልከለከልህምና፡**

**በእውነት በረከትን እባርክሃለሁ፡ ዘርህንም እንደ ሰማይ ከዋክብትና፡ በባሕር ዳር እንዳለ** አሸዋ **አበዛዋለሁ፣ ዘርህም የጠላቶችን** ደጅ **ይወርሳል፣**

**የምድር አሕዛብ ሁሉም በዘርህ ይባረካሉ፣ ቃሌን ሰምተሃልና።**

2 በመታዘዙ፡ እንዴት ያለ በረከት ነው ያገኘው! እግዚአብሔር የሚፈልገው መታዘዝን ነው። በአንድ ወቅት፡ "መታዘዝ ከመሥዋዕት ይበልጣል" ተብሏል። እግዚአብሔርን መታዘዝ ማድረግ ከምትችሉት ከየትኛውም መሥዋዕት ይበልጣል።

3 ዛሬ ማታ፡ "የእምነት አባት" ተብሎ ስለተጠራው፡ **የአባቶች አለቃ አብርሃም፡** በሚል ታላቅ ርዕሰ አሁን እንነጋገራለን፡ ምክንያቱም እግዚአብሔር ለእርሱና ለዘሩ፡ ምድርን እንዲወርሱ ቃል ገብቶላቸዋልና። እኛም በአብርሃም በኩል፡ በክርስቶስ ሞተን፡ የአብራሃም ዘሮቹ ሆነናል ለእርሱም የተሰጡት ተስፋዎች ተካፋዮች ሆነናል።

4 አሁን፡ አብርሃም ተራ ሰው ነበር፡ የተለየ ነገር አልነበረውም። ከቅዱሳት መጻሕፍት እንደምናውቀው፡ አብርሃም ሰባ-አምስት ዓመት እስኪሞላው ድረስ፡ እግዚአብሔር አልጠራውም። ሚስቱ፡ ግማሽ እኅቱ የነበረች ስትሆን፡ በጊዜው ዕድሜዋ ስልሳ-አምስት ዓመት ነበር፡ ምናልባትም ከልጅነታቸው ጀምሮ አብረው ኖረው ሊሆን ይችላል። እሷም መካን ስለነበረች፡ ልጅ አልነበራትም ነበር። እግዚአብሔር ከሌላው ዓለም ለመለየት፡ ሙሉ በሙሉ ከህዝቦቹ ሁሉ፡ ከዘመዶቹ ሁሉ ሊለየው ፈልጎ፡ በፍጹም መለየት ጠራው። ማድረግ ያለበት ልዩ ነገር ነበረው።

5 እግዚአብሔር አንድ የተለየ ነገር እንድታደርጉ ሲፈልጋችሁ፡ ከማንኛውም ጥርጣሬ ሙሉ በሙሉ እንድትለዩ ይፈልጋል። እሱ የሚናገረውን ለመታዘዝ፡ ወደ ሙሉ ታዛዥነት መምጣት አለባችሁ። እግዚአብሔር ያንን ይፈልጋል። በሌላ መንገድ ልታደርጉት አትችሉም። ስለዚህ፡ አሁንም፡ ሁልጊዜ ምሳሌን ያስቀምጣል፡ እግዚአብሔር አብርሃምን ለእግዚአብሔር የተለየ ሕይወት እንዲኖር፡ ከቤተሰቡና፡ ከዘመዶቹ ሁሉና፡ ከመሳሰሉት ሙሉ ለሙሉ እንዲለይ መጥራቱ፡ ምሳሌ ነበር።

6 ዓመታት አለፉ፡ ምንም ነገር አልሆነም፡ አብርሃም ግን አሁንም ቀጠለ። ተስፋ አልቈረጠም። "ለእግዚአብሔርም ክብር እየሰጠ በእምነት በረታ እንጂ፡ በአለማመን ምክንያት፡ በእግዚአብሔር ተስፋ ቃል በፍጹም አልተጠራጠረም።"

7 ዓመታት፡ እያለፉ ሲሄዱ፡ ብዙ ተቺዎች መምጣታቸው አያጠራጥርም፡ "የሕዝብ አባት አብርሃም ሆይ፡ አሁን ስንት ልጆች አሉህ? " እያሉ ተሳለቁበት፡ ያ ግን እንዲጠራጠር አላደረገውም። ልጅ የለም፡ ሣራ መውለድ ከምትችልበት እድሜ ገደብ አልፋለች፡ ልጆች ከመውለድ፡ እርግጥ ነው፡ ካረጠች ብዙ ቆይታለች፡ ነገር ግን አሁንም አብርሃም እግዚአብሔርን ከዚህ በፊት እንደሚያምነው ሁሉ አመነ። ለሚወለደው ህጻን ዝግጅት አደረገ፡ ምክንያቱም እግዚአብሔር የማይፈጽመውን ትልቅ ተስፋ ሊሰጥ እንደማይችል ያውቅና ሙሉ በሙሉ ያምን ነበር።

8 ዘሩም እንዲሁ ማሰብ አለበት። በተፈጥሮአዊ አእምሮ ውስጥ ምንም ያህል እውነት የማይመስልና፡ ተፈጥሮአዊ ያልሆነ ቢመስልም፡ እግዚአብሔር ሊፈጽመው የማይችለውን ቃል ሊገባ አይችልም። ዛሬም ያንን ተመሳሳይ ነገር እናምናለን። እያንዳንዱ እውነተኛ የአብርሃም ዘር ተመሳሳይ ነገር ያምናል። ምንም ዓይነት ሁኔታ ቢያጋጥመን፡ ምንም ያህል እውቀት ብናከማች፡ ምንም ያህል ነገሮች ቢሆኑ፡ ለተፈጥሮአዊ አእምሮ ምን ያህል ተፈጥሮአዊ ባይመስልም፡ እንዲያውም፡ በተፈጥሮአዊ አእምሮ፡ ምንም ያህል ሞኝነት ቢመስልም፡ ምንም ለውጥ አያመጣም። እግዚአብሔር ከተናገረ፡ ይፈጸማል በቃ። የአብርሃም ዘሮች **የሰራዊት ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል** በሚለው የተረጋጉ ናቸው። ይኸው ነው።

9 ከዚያም ከሀያ-አምስት ዓመት በኋላ፡ ምንም ልጅ እንደሌለው፡ እናያለን። አሁንም እግዚአብሔር ለአብርሃም የገባውን ቃል ለመጠበቅ ታማኝ ነበር፡ ምክንያቱም አብርሃም በእግዚአብሔር ታምኗልና። ትንሹ ወንድ ልጅ ተወለደ፡ ህጻኑ ይስሐቅ መጣ።

10 ከዚያም ህጻኑ ይስሐቅ ከመጣ በኋላ፡ ከዚያም እግዚአብሔር በድርብ ፈተና ፈተነው። እንዲህ አለ፡ "ይህ ልጅ... " አብርሃም አሁን መቶ አሥራ አምስት፡ ወይም መቶ ሀያ ዓመት ገደማ፡ ከሆነው በኋላ። እንዲህ አለ፡ "ልጅህን፡ አንድ ልጅህን፡ እኔ ወደማሳይህ ተራራ ውሰደው፡ በዚያም በዚህ ተራራ ላይ፡ መሥዋዕት አድርገህ፡ አቅርበው።" በሌላ አነጋገር፡ የገባው ቃል እንደሚፈጸም የሚያሳይ ማስረጃ ሁሉ ማጥፋት ማለት ነው። ይህ ደግሞ እንድናምን የሚያደርጉንን ተፈጥሯዊ ነገሮችን በሙሉ ያጠፋዋል።

11 አብርሃምም እንዲህ አለ፡ "ልጄን ከሙታን እንደ ተነሣ አድርጌ ነው የተቀበልኩት። እርሱም ከሙታን ሊያስነሣው እንደሚችል ሙሉ በሙሉ ተረድችያለሁ።

12 ይህ ሕዝብ አሁን የአብርሃም ዘር ነው፡ ምክንያቱም እርሱ ከሙታን አስነስቶናል። በኃጢአታችንና በበደላችን ሞተን ነበርን። አእምሮየን ለመለወጥ፡ ሃሳቤን ለመለወጥ፡ ፍጥረቴን ለመለወጥ፡ ሙሉ በሙሉ ሊለውጠኝ የቻለው እሱ፡ የፈለገውን ማድረግ ይችላል። የሚናገረው ሁሉ፡

እውነት ነው ብዬ አምናለሁ፡ እያንዳንዱ የአብርሃም ዘርም ተመሳሳይ ነገር ያምናል።

13 አብርሃም፡ እግዚአብሔርን በመታዘዙ፡ ትንሹን ልጁን ወሰደ። ልጁን በሚወስድበት ጠዋት፡ አገልጋዮቹን እንዲህ አላቸው፡ "እናንተ ከበቅሎዎቹ ጋር እዚህ ጠብቁን። እኔና ልጄ ወደዚያ ተሻግረን መሰዋዕት እናቀርባለን፡ ከዚያም እሱና እኔ እንመለሳለን።" ኡህ፡ እንዴት ሊያደርገው ነው? የገዛ ልጁን ሕይወት ለማጥፋት፡ ወደ ተራራው አናት እየወጣ ነው፡ ነገር ግን እንዲህ ይላል፡ "ህጻኑ፡ ልጄና እኔ እንመለሳለን" ይላል። አንድ ነገር መሆን እንዳለበት ያውቅ ነበር። እግዚአብሔር እንዴት እንደሚያደርገው አያውቅም ነበር፣ ያ ጥያቄው አልነበረም። እግዚአብሔር ቃል እንደገባው ያውቃል።

14 ማወቅ ያለብን ነገር ይህ ብቻ ነው፡ እግዚአብሔር ቃል ገብቶታል! እንዴት ሊሆን ይችላል? ይህን ልነግራችሁ አልችልም። ነገር ግን እግዚአብሔር ተናግሯል! ለሁለተኛ ጊዜ፡ ኢየሱስ ክርስቶስን ይልካል፡ በአካል ይመጣል። የእርሱ የሆኑትን ይሰበስባል። በዚህ ምድር ላይ ከእሱ ጋር፡ ከዳኑት ጋር፡ አንድ ሺህ ዓመት፡ የሺህ ዓመት ግዛት ይኖራል። እግዚአብሔር ቃል የገባው ይህን ነው፡ እኛም ይህ ቀን እንዲመጣ እንጠባበቃለን።

15 የታመሙትን ለመፈወስ፡ የሞቱትን ለማስነሳት፡ አጋንንትን ለማስወጣት ቃል ገብቷል። እንደሚያደርገው ቃል ገብቷል። ትናንት፡ ዛሬና ለዘላለም ያው ነው። እንዴት? አላውቅም። ይህን ለማድረግ ቃል ገብቷል! ይህን እናምናለን፡ በቃ ያ ያረጋግዋል። አንድ ሰው እግዚአብሔርን ሲያምን፡ የሚናገረውን ሁሉ ያምናል።

16 አብርሃምም እግዚአብሔርን ያመነበት እንደዚህ ነው። አሁን የገባው ቃል እንደሚፈጸም የሚያሳይ ማስረጃ ሁሉ እንዲያጠፉ ተጠይቆ ነበር፡ ነገር ግን እግዚአብሔር ይህን ማድረግ እንደሚችል እርግጠኛ ነበር።

17 አሁን፡ ይህን ታላቅ ተስፋ የሰጠው ለእርሱ ብቻ ሳይሆን፡ ለዘሩም፡ ጭምር ነው። አብርሃም ታማኝ ስለነበርና፡ እግዚአብሔር የገባለትን ቃል ጠብቆ ስለነበር፡ እግዚአብሔር ልጁን ከሞት ማስነሳት እንደሚችል ያውቅ ነበር። ለገዛ ልጁ አልራራም፣ ነገር ግን (እግዚአብሔር) እርግጥ ነው፡ እንዲያ ልጁን የሚሰጥ አይነት አምላክ ነው፣ እንጨቱን ተሸክሞ ወደ ተራራ እንደወጣና፡ የመሳሰሉትን እንዳደረገ፣ ክርስቶስም በኋላ የራሱን መስቀል ተሸክሞ፡ ወደ ተራራው፡ ወደ ተሰቀለበት ቦታ ወጣ።

18 አብርሃም ይህን በማድረጉ፡ በምድር ላይ ካለው ከማንኛውም ነገር በላይ፡ ሌላው ቀርቶ ከአንድያ ልጁ በላይ አስበልጦ እግዚአብሔርን ስለወደደው፡ ያ እግዚአብሔርን በጣም ደስ እንዳሰኘው እንገነዘባለን። ማንም ሊናገረው ከሚችለው በላይ፡ ማንም ሊያደርገው ከሚችለው በላይ፡ ቃሉን እስኪያምን ድረስ እግዚአብሔርን ይወደው ነበር።

19 የአብርሃም ዘር ሁሉ እግዚአብሔርን የሚያምነው በዚህ መንገድ ነው። እግዚአብሔርን ያምናሉ። ይህም እግዚአብሔርን በጣም ደስ እንዳሰኘው እናውቃለን ስለዚህም እንዲህ አለ፡ "ዘርህም የጠላቶችን ደጅ ይወርሳል። ዘርህም የጠላቶችን ደጅ ይወርሳል።" አስታውሱ፡ ያ **የሰራዊት ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል** ነው። የአብርሃም ዘር ይህን ያምናል።

እውነተኛ የአብርሃም ዘር ከሆናችሁ፡ የአብርሃም እምነት፡ በእናንተ ውስጥ ይኖራል። እግዚአብሔር የተናገረውን ታምናላችሁ፡ እግዚአብሔርም ቃል ኪዳኑን ይጠብቃል።

20 ተናግሯልም፡ አሁን አስታውሱ፡ እግዚአብሔር አብርሃምን ከፈተነው በኋላ ነው ይህን ቃል ኪዳን የገባላት። በእውነቱ ቃሉን እንደሚያምኑ ለማየት፡ የአብርሃም ዘር በመጀመሪያ መፈተን አለበት። አስታውሱ፡ የእግዚአብሔርን የተሰፋ ቃል መጠበቅ የሚችለው ብቸኛው መንገድ፡ እርሱ በእግዚአብሔር የተሰፋ ቃል ሰላመነ ነው፡ ስለዚህ እንዳመነና እንዳላመነ ለማረጋገጥ ተፈተነ።

21 ወደዛ ፈተና መጥተናል። ዛሬም፡ የአብርሃም ዘር፡ በዚህ ፈተና ላይ እንገኛለን። የእግዚአብሔርን ቃል እንወስዳለን፡ ወይስ ስለ እግዚብሔር ቃል ሰው የተናገረውን እንወስዳለን? አንድ ድርጅት እንደ ሐይማኖት መገለጫ ያቀረበውን ትምህርት፡ እንቀበላለንን፡ ወይስ እግዚአብሔር የተናገረውን እንቀበላለን? የእግዚአብሔር ቃል እውነት ከሆነ፡ ሌላ ማንኛውም ነገር ምንም ይሁን ምን፡ የእግዚአብሔርን ቃል እናምናለን። የሰው ቃል ሁሉ ውሸት ይሁን፡ የእግዚአብሔርም ቃል እውነት ይሁን። እውነተኛው የአብርሃም ዘር! ግን እውነተኛው ዘር ከመሆናችሁ በፊት፡ ልክ አብርሃም ራሱ፡ እንዳደረገው፡ በፈተና ማለፍ አለባችሁ። እግዚአብሔር ለአብርሃም ብቻ ሳይሆን፡ ዘሩ የጠላቶቹን ደጆች እንደሚወርስ ቃል ገብቶለታል። ኦህ፡ ማይ!

22 እስቲ አስቡት፡ የአባቶች አለቃ ሙሉ በሙሉ እርግጠኛ ነበር፡ በእግዚአብሔር ተሰፋ ቃል ሲፈተን ትክክል፡ ትክክል ነበር። ሁኔታው ምንም ይሁን ምን፡ ቃሉ ትክክል እንደሆነ አመነ። አብርሃም፡ ታላቁ የአባቶች አለቃ፡ በፈተና ጊዜ፡ በእምነቱ አልተዳከመም። እግዚአብሔር ከሞት ሊያስነሣው እንደሚችል አመነ። አመነ፡ ምክንያቱም እግዚአብሔር ቃል ገብቷልና። እግዚአብሔርም “የአሕዛብ አባት፡” እንደሚሆን ቃል በገባለት ጊዜ ይህ እንደሚሆን አመነ። እንዴት እንደሚሆን አያውቅም ነበር። ካመነ በኋላ፡ ከሀያ-አምስት ዓመታት በኋላ፡ ሕፃኑ ሲወለድ፡ ሕፃኑን እንዲያጠፋው ሲጠየቅ፡ አሁንም የእግዚአብሔር ተሰፋ እውነት መሆኑን አውቆ፡ ልጁን ሰጠ።

23 ዘሩ፡ ተመሳሳይ ነገር ያደርጋል! የአብርሃም ዘር ለሆኑ ሰዎች፡ የእግዚአብሄር ቃል ኪዳን ማኅተም ይሆናል። ቃል ኪዳኑ ማኅተም፡ የተፈረመበት ምስክር ነው። ቃል የተገባውን ቃል ሁሉ ሰናምን፡ ተሰፋውን ለማረጋገጥ፡ ያ ማህተም ይሰጠናል። አያችሁ፡ የ—የአብርሃም ዘር እንደመሆናችን መጠን፡ መጽሐፍ ቅዱስን፡ እንደምናምንና፡ እንደማናምን ለማየት በፈተና ውስጥ እናልፋለን፡ መጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔር ቃል ነው፡ ምክንያቱም እርሱ እግዚአብሔር ራሱ ነው፡ ስለዚህ ያንን ለማመን፡ በፈተና ውስጥ ማለፍ አለባችሁ።

24 አንዳንዶቹ፡ “የተአምራት ዘመን አልፏል” ሲሉ፡ ያንን ከተቀበላችሁ፡ ከቃሉ ጋር የሚቃረን ነው።

25 እንዲህ ካላችሁ፡ “ዛሬ፡ መንፈስ ቅዱስን አንቀበልም። እንዲህ ያለ ነገር የለም። አሥራ ሁለቱ ሐዋርያት ብቻ ናቸው የተቀበሉት።”

26 ቃሉ እንዲህ ይላል፡ ሐዋርያው ጴጥሮስ በጴንጠቆስጤ ዕለት ሲሰብክ፡ እንዲህ አለ፡ “ንስሐ ግቡ፡ ኃጢአታችሁም ይሰረይ ዘንድ፡ እያንዳዳችሁ

በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ተጠመቁ፡ የመንፈስ ቅዱስንም ስጦታ ትቀበላላችሁ። የተሰፋው ቃል ለእናንተና፡ ለልጆቻችሁ፡ እንዲሁም ጌታ አምላካችን ወደ ራሱ ለሚጠራቸው፡ በሩቅ ላሉ ሁሉ ነው።"

27 ቃሉ በትክክል የሚለው ያንኑን ነው። ይህም፡ አሁን ፈተናውን ለመውሰድ፡ የእግዚአብሔር የሚፈትናችሁን ፈተና ለመውሰድ ዝግጁ ከሆናችሁ፡ ያንን መምሪያ ተከተሉ፡ እነግራችኋለሁ፡ ካመናችሁ፡ እግዚአብሔር ቃሉን እንደሚጠብቅ ታያላችሁ። በትክክል። ነገር ግን ያንን ማለፍ አለባችሁ፡ ምክንያቱም ያ ማህተም ነው፡ ያንን መቀበል ስትችሉ፡ ያን ጊዜ ተሰፋውን ትቀበላላችሁ። ምክንያቱም፡ የእግዚአብሔር መምሪያ ነው፡ ማድረግ ያለብን፡ መከተል ያለብን፡ የተናገረውን ብቻ ነው። አሁን ለአንዳንዶች ብቻ አይደለም፡ ነገር ግን "ለሚያምን ሁሉ፡" ለሚያምን ሁሉ፡ ንስሐ ለገባ ሁሉ፡ ለምያምን ሁሉ ነው። ለሁሉም ትውልድ ነው፡ ለሁሉም ሕዝብ ነው፡ ለማመን ለሚፈልግ ሁሉ ነው። በእግዚአብሔር ቃል ላይ ያላችሁ እምነት ወደዚህ ተሰፋ ያመጣችኋል። ከዚያ በኋላ፡ ይህን ስታደርጉና፡ ስታደርጉ ብቻ ነው የቃል ኪዳኑን ማኅተም የመያዝ ሥልጣን የሚኖራችሁ።

28 የምንቀበለው የተሰፋው ቃል፡ ማኅተሙ፡ የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት ነው። በትክክል። ቃሉ በውስጣችሁ ሲኖር፡ እግዚአብሔር በመንፈስ መልክ ሆኖ፡ ወደ ውስጣችሁ ይመጣል። ቃሉን በውስጣችሁ ከተቀበላችሁ፡ ያንን ቃል በውስጣችሁ ሕያው ሊያደርገው የሚችል ብቸኛው ነገር መንፈስ ቅዱስን ብቻ ነው፡ ከዚያም ሊያጠቃችሁ የሚሞክረውን የጠላት ደጅ ሁሉ የመውረስ የተሰፋ ቃል ይኖራችኋል። በትክክል። እግዚአብሔር ቃል ገብቷልና፡ እንደዚያው ይሆናል።

29 አሁን፡ አስታውሱ፡ ይህን ማድረግ የምትችሉት፡ በቃሉ ከተፈተናችሁና፡ ከተፈተናችሁ በኋላ ብቻ ነው።

30 አብርሃም በቃሉ ተፈተነ። "አብርሃም ሆይ፡ ልጅ እንደምትወልድ፡ ታምናለህን? "

"አዎን።"

31 ልጁ መጣ። "አሁን ልጁን አስወግደው። አብርሃም ሆይ፡ አሁንስ ታምናለህን? "

32 "አንተ ከሙታን ልታስነሣው ስለምትችል፡ አሁንም፡ አምናለሁ" አለ።

33 ከዚያም በኋላ፡ እንዲህ አለ፡ "አሁን፡ ዘሮችህ የጠላቶቻቸውን ደጅ ይወርሳሉ" አለ። አሜን! ከፈተና በኋላ!

34 እስቲ የአብርሃምን ዘር፡ በሥጋ በኩል ዘሩን እንመልከት። ይህም፡ እኛ ዛሬ መንፈሳዊ ዘር ነን። ነገር ግን በሥጋ የአብርሃም ዘር የሆኑት፡ ሙሉ የእግዚአብሔርን ተሰፋ እንዳመኑ፡ እንመልከት፡ እናም በፍጹም-... [በቴፕ ላይ ባዶ ቦታ አለ—አርታዒ።]

35 እኔም፡ "በነገራችን ላይ፡ ለምንድነው አንዲት ክርስቲያን ልጃገረድ ውስጥ ልብሷን ማሳየት የምትፈልገው? ሊገባኝ አልቻለም" አልኩ።

36 ከእግዚአብሔር፡ ዳግመኛ ተወልዳችሁ፡ ማን እንደሆናችሁ ለማሳየት የመንፈስ ቅዱስ ውበት አላችሁ። እናንተ፡ እነዚህ የማይረቡ ቀሚሶች

የሌሏቸውን በጎነት አላችሁ፡ በትክክል፡ እውነተኛ የእግዚአብሔር ሴት፡ በጎነት ጐልቶ ይታይባታል፡ ሊሳቅባችሁ ይችላል፡ እንዲሁም አሮጌ ፋሽን ልትባሉ ትችላላችሁ፣ ነገር ግን ሊነኩት የማይችሉት ነገር አላችሁ፡ እንደ አጥተዋልና እንደገና በጭራሽ ማግኘት አይችሉም። በትክክል። በጎነት አላችሁ። እግዚአብሔር የሚፈልገው፡ በጎነትን ነው። አያችሁ?

37 ነገር ግን ማድረግ ያለባችሁ የመጀመሪያው ነገር፡ በአዕምሩዋችሁ ውስጥ ጥያቄ ካለ፡ በጭራሽ አታድርጉት። በአዕምሮአችሁ ውስጥ ጥያቄ ካለ ወደ ጸሎት መሰመር እንዳትመጡ። ሙሉ በሙሉ እስካላመናችሁ ድረስ፡ ምንም ጥርጣሬ፡ በአዕምሯችሁ ውስጥ ምንም ዓይነት የጥርጣሬ ሃሳብ እስካለ ድረስ፡ በጭራሽ እንዳትመጡ፡ ነገር ግን እንደምትፈወሱ አምናችሁ ኑ፡ ከዚያ ከዚህ መድረክ ተፈውሳችሁ ትወርዳላችሁ። በትክክል፡ ያ የሚሆነው በጭንቅላታችሁ ላይ ምንም አይነት ጥያቄ፡ በጭራሽ ምንም ጥርጣሬ ሳይኖር ሲቀር ነው። እግዚአብሔርን ማመን አለባችሁ፡ አስመሳይ-አማኝነት አይሁን። በእውነት እመኑት!

38 የአብርሃም ዘር የሚያምነው ቃሉ ስለተናገረ ነው፡ እኛም የምናምነው ለዚህ ነው። አንድ ሰው ስለተቸ አይደለም የምናምነው፡ ምክንያቱም የሆነ ሰው ነው የተናገረውን። እግዚአብሔር ስለተናገረ እናምነዋለን፡ ያ እውነት ያደርገዋል። እግዚአብሔር ሲናገር፡ ሁሉንም ጥያቄዎችን ይመልሳል። እርሱ የመጨረሻው ቃል ነው። እርሱ መደምደሚያ ነው። እግዚአብሔር አንድ ሲናገር፡ ያ ነገሩን ያረጋግዋል። ምንም ለእርሱ በተቃራኒ ልናገር አይችልም። “የሰው ሁሉ ቃል ውሸት ይሁን፡ ቃሌ እውነት ይሁን።”

39 አሁን ከእነዚህ ዘሮች መካከል የተወሰኑትን ስንመለከት፡ እስቲ እናስብ። የዕብራውያንን ልጆች እናስብ፡ እዚህ፡ ስለ ዕብራውያን ልጆች፡ እያሰብኩ ነው፡ ከጣዖት አምልኮ ጋር በተያያዘ ከተፈተኑ በኋላ ምን እንደሆኑ። አሁን፡ አስታውሱ፡ ንጉሡ እንዲህ አለ፡ “ለዚህ ምስል የማይሰግድ ሁሉ፡ ወደ እቶን እሳት ይጣላል።” አሁን፡ እነዚህ ልጆች የእግዚአብሔር ቃል ትክክል ነው ብለው ያምኑ ነበር፡ ምንም ዓይነት ምስል ማምለክ የሌብንም ብለው ያምኑ ነበር፡ ነገር ግን ወደ ክስተቱ ሲመጡ ማድረጋቸውንና አለማድረጋቸውን ለማረጋገጥ ተፈተኑ።

40 ሌሎቹ ልጆች፡ አምልኮውን ተቀብለው ለምስሉ ለመሰገድ ሄዱ፡ ንጉሡ ባዘዘው መንገድ ለምስሉ ለመሰገድ ሄዱ። ግዴታ ማድረግ ያለባቸውን፡ በጊዜው ታዋቂ የሆነውን ሃሳብ ደግፈው ለምስሉ ለመሰገድ ሄዱ።

41 ለምስሎች ይሰግዱና የእግዚአብሔርን ቃል ያፈርሱ ይሁን ተብለው፡ ሲፈተኑ፡ ለቃሉ ታማኝ ሆነው ቆሙ። ሁኔታዎች ምንም ቢሆኑም፡ ለቃሉ ታማኝ ሆነው ቆይተዋል። ወደ እሳቱ እቶን ሲጥሏቸው፡ የእግዚአብሔር ቃል ኪዳን ተፈጸመ። የጠላቶቻቸውን ደጆች ወረሱ። በእሳት ውስጥ ያለውን የማቃጠል ሃይል የሚያስወግድ ቍልፍ የያዘ፡ አራተኛ ሰው እዚያ ቆሞ ነበር፡ እነሱን ነጻ ከማውጣት በስተቀር ምንም ማድረግ አልቻለም። አሜን።

42 አንድ ወንድ ወይም አንዲት ሴት ፈተናውን ለመውሰድ ዝግጁ ሲሆኑ፡ የስርቶ ማሳያ ፈተና!

43 እያችሁ፡ ወደ እሳቱ ውስጥ መግባት ነበረባቸው፡ ሲገቡም፡ በእሳቱ ውስጥ ነበሩ፡ የሆነው ብቸኛው ነገር፡ ይህ የእሳቱ ፈተናው፡ እጃቸውን ከ—ከእስራት ፈታላቸው።

44 አብዛኛውን ጊዜ፡ እግዚአብሔር፡ እኛ በዓለም ነገር ስንያዝ፡ ስንተሳሰር፡ ውሳኔ መወሰን ወዳለብን ደረጃ እንድንደርስ፡ ከባባድ ፈተናዎች እንዲደርሱብን ይፈቅዳል። ያንን ስናደርግ፡ ፈተናው ሊያደርገው የሚችለው ብቸኛው ነገር፡ እውነተኛ የአብርሃም ዘር በ—በውሳኔ መሰቀለኛ መንገድ ላይ ቆሞ፡ እግዚአብሔርን ለማገልገል ይወስናል፡ ማሰሪያዎቹን ፈቶ ነጻ ያወጣናል። ሰይጣን በሽታ ሊሰጣችሁ ይችላል። ሌላ ነገርም ሊሰጣችሁ ይችላል፡ ሌላ ነገር። ምን ዓይነት ውሳነ እንደምትወስን ለማየት፡ እዚያ መሰቀለኛ ሁነታ ውስጥ ያስቀመጠህ እግዚአብሔር አ—አ—አለመሆኑን በምን ታውቃላችሁ?

45 የእሳቱን ደጅ ወረሱ። እሳቱ ሊያቃጥላቸው አልቻለም። የእሳቱ ሽታ እንኳን አልነካቸውም፡ ምክንያቱም የአብርሃም ዘር መሆናቸውን ያውቁ ነበር፡ ለእግዚአብሔርና ለቃሉ ታማኝ ነበሩ። የጠላትን ደጆች ወ—ወረሱ፡ እሳቱም ሊያቃጥላቸው አልቻለም፡ ምክንያቱም ደጆችን ወርሰዋልና።

46 ከጊዜ በኋላ፡ አንድ ሰው ነበረ፡ ዳንኤል የሚባል፡ አንድ ነቢይ በዚያ ነበር። እ... እርሱም እውነተኛውን አምላክ እንደሚያገለግልና እንደማያገለግል ተፈተነ። አንድ የሆነውን እውነተኛ አምላክን እንደሚያገለግል፡ ወይም አረማዊውን አምላክ እንደሚያመልክ፡ መወሰን የነበረበት ጊዜ ሲመጣ፡ አርማዊውን አምላክ እምቢ አለና፣ መስኮቶቹን እየከፈተ፡ በየቀኑ፡ ወደ አምላኩ ጸለየ። በፌዴራል ህጎች መሰረትም፡ ተይዞ፡ ወደ አንበሶች ጉድጓድ ተጣለ። የተራቡ አንበሶች ተከትለውት ጮኹ። ምን አደረገ? የጠላቶቹን ደጅ ወረሰ። አንበሶቹም ሊበሉት አልቻሉም። እግዚአብሔርም በእሱና በአንበሳው መካከል የቆመውን መልአክ፡ የእሳት አምድ ላከ።

47 የጠላትን ደጅ ወረሰ፡ ምክንያቱም አንድን እውነተኛ አምላክ እንደሚያመልክ፡ ወይም የሚመለኩትን በደርዘን የሚቈጠሩ አረማውያን አማልክት እንደሚያመልክ ለማየት ተፈተነ። ስለዚህ ፈተናውን ተቋቁሞ፡ የጠላትንም ደጅ ወረሰ። እግዚአብሔር ከእርሱ ጋር ስለ ነበረ፡ አንበሳው ሊነካው እንኳ አልቻለም። የአብርሃም እውነተኛ ዘር ስለነበር፡ እግዚአብሔር የገባው ቃል እውነተኛ ሆኖ ጸና።

48 ሙሴ፡ ኦህ፡ ሌላ ታላቅ ሰው ነው። እርሱም፡ እግዚአብሔር የሰጠውን ተስፋ ለማየት፡ ተፈተነ። “ወደዚያ ስትወርድ አብሬህ እሆናለሁ።” እግዚአብሔር የሰጠውን ስጦታውን የሚያስመስሉትን ሲገጥማቸው፡ ያኔስ እና ያምብሬስ ተነሥተው ሙሴ እንዲያደርግ የታዘዘውን ነገር ለማስመሰል ሞከሩ። እግዚአብሔርም ጠርቶታል፡ ይህን ለማድረግ የተሾመው እርሱ መሆኑን አወቀ፡ እዚያም ቆሞ እግዚአብሔር እንዳዘዘው ተኣምራቱን አደረገ። እነሆም ተመሳሳይ ነገር ለማድረግ፡ አስመሳዮች ቆመው ነበር፡ ነገር ግን ያ ሙሴን አላስጨነቀውም። ለእግዚአብሔር ቃል ታማኝ ሆኖ ቆመና፡ የጠላትን ደጅ ወረሰ፡ አሜን፡ ወረሰ፡ ምክንያቱም እሱን ለማስመሰል የሚሞክር ማንም ይሁን ማን፡ ለእግዚአብሔር ተስፋ ቃል ታማኝ ሆኖ ቆመ።

49 ይህ ለእያንዳንዱ ክርስቲያን እንዴት ያለ ትምህርት ነው! ዙሪያችሁን ስትመለከቱና ግብዝ ስትመለከቱ፡ እውነተኛን ሃሳብ ለማስመሰል እየሞከረ መሆኑን ብቻ አስታውሱ። ነገር ግን፡ ይህ ማለት አንድ እውነተኛ አለ ማለት ነው። ለእግዚአብሔር ቃል ታማኝ ሁኑ! ምንም ቢመጣ ወይም ቢሄድ ችግር የለውም፡ ቃል ክዳኑን ጠብቁ። አዎን፡ ዳንኤል ለእግዚአብሔር ቃል ታማኝ ሆኖ ቆየ።

50 ምንም እንኳን ብዙዎች እሱን ለማስመሰል ቢሞክሩም፡ ሌሎች ነገሮችንም ለማድረግ ቢሞክሩም፡ እሱ እውነተኛ ሆኖ ቆየ። እሱ ለአንድ ዓላማ ነው የመጣው፡ እስራኤልን ከግብፅ ለማውጣትና፡ ሕዝቡን ወደ ተስፋይቱ ምድር ለመውሰድ ነው የመጣው። ከግብፅ ወጥተው፡ ወደ ተስፋይቱ ምድር እየሄዱ ሳለ፡ የሙት ባህር በመንገድ ላይ ገጠማቸው። የውኃውን ደጆች ወረሰ፡ በሮቹም ለሁለት ተከፈሉ። ውኋውም ወ––ወደ ኋላ ተመለሰ፡ ሙሴም እስራኤልን ወደ ምድረ በዳ፡ እግዚአብሔር ወዳዘዘው ተራራ ወሰዳቸው። አሜን። የጠላትን ደጅ ወረሰ።

51 አባቱ፡ አብርሃም፡ እውነተኛ ዘሩ የጠላትን ደጅ እንደሚወርስ፡ የተስፋ ቃል ተሰጥቶት ነበር። የውኃው ደጆች ተዘግተው ስለነበር፡ ሊሻገር አልቻለም ነበር፡ ያ የግዳጅ መንገዱ ነበር። እነዚያን ልጆች ወደ ተራራው ማምጣት ነበረበት። እግዚአብሔርም እንደዛ እንዲያደርግ ነግሮታል። ደጅ በመንገዱ ላይ አጋጠመው፡ እርሱም የጠላትን ደጅ ወረሰ።

52 ከትንሽ ጊዜ በኋላ፡ ኢያሱ፡ ወደ ቃዴስ-በርኔ ሲደርሱ፡ ሰፍራውም ያን ጊዜ የዓለም የፍርድ ወንበር ነበረና፡ በዚያ እስራኤል ፍርዷን ተቀበለች። ኢያሱ ከካሌብ ጋር ሲሆን፡ ሌሎች አሥራ ሁለት... ወ––ወይም አሥር ሰዎችም አብረውት ነበሩ። ከእያንዳንዱ ነገድ አንዳንድ ሰው ምድሪቱን ለመሰለል ተልኮ ነበር።

53 እነዚያን ታላላቅ ግዙፍ ሰዎች እዚያ ቆመው ሲያዩ፡ አሥሩ በጣም መጥፎ ስሜት ተሰማቸው፡ እንዲህ አሉ፡ “መውረስ አንችልም። በጣም ትልቅ ነው። ለምን፡ ተመልከቱ የሚቃረኑን” አሉ። ነገር ግን ሪፖርቱን ይዘው ሲመለሱ፡ ክፉ ሪፖርት ይዘው መጡ።

54 እግዚአብሔር፡ “ይህችን ምድር ለእናንተ ሰጠኋት፣ የእናንተ ናት” ካላቸው፡ ለምን መጥፎ ወሬ ይዘው ተመለሱ? እዚያ በግብፅ እንዲህ አላቸው፡ “ይህችን ወተትና ማር የምታፈስሰውን፡ መልካም ምድር፡ ይህች ምድር ለእናንተ ሰጥቻችኋለሁ።”

55 ይሁን እንጂ ተቃውሞው በጣም ከባድ መሆኑን ሲመለከቱ፡ አሥር የሚሆኑት ተመልሰው መጡና፡ “ይህን መውረስ አንችልም” አሉ።

56 ኢያሱ ነበር፡ ህዝቡን ያረጋጋቸው፡ እንዲህ በማለት፡ “እኛ ይሄን ለመውረስ ከበቂ በላይ አቅም አለን። ከበቂ በላይ አቅም አለን!” ምክንያቱም ለምን? የተስፋውን ቃል እየተመለከተ ነበር። እርሱ የአብርሃም እውነተኛ ዘር ነበር። ተቃውሞው ምንም ይሁን ምን፡ “የከተማውን ደጅ መውረስ እንችላለን፡ ምክንያቱም እግዚአብሔር ምድሪቱን እንደሚሰጠን ቃል ገብቶልናል።” እርሱም ደጁን ወረሰ።

57 በኋላም፡ የእስራኤልን ልጆች ወደ ወንዙ ሲያወርዳቸው። የሚያዝያ ወር፡ ታላቁ የዮርዳኖስ ወንዝ፡ ሞልቶ፡ ጠበቃቸው። ዮርዳኖስ ከተራሮች እናት ላይ

ወርዳ፡ በሜዳዎቹ መካከል ተዘርግታለች። ያም ለእርሱ፡ እሱ በዚያ መገኘቱ፡ የዓመቱ መጥፎ ቀን፡ ይመስላል። ሆኖም፡ ግን፡ የአብርሃም ዘር ነበር። የተሰፋ ቃል እንዳለው ያውቅ ነበር፡ በግዳጅ ላይ ነበር። እግዚአብሔር እንዴት ማድረግ እንዳለበት፡ ራእይ ሰጠው፡ የወንዙንም ደጆች ወረሰ። የውሃው ደጆች በተከፈቱ ጊዜ፡ ውኃው ወደ ተራራዎች ተመልሶ ፈሰሰ። ኢያሱና እስራኤላውያን የጠላትን ደጅ ወርሰው፡ ወደ ተሰፋይቱ ምድር ተሻገሩ፡ ምክንያቱም እግዚአብሔር እንዲህ እንዲያደርጉ ነግሯቸዋልና። እውነተኛ የአብርሃም ዘር!

58 ወንድሞቼና እኅቶቼ፡ ወደዚያ ሲደርስ፡ ኢያሪኮ ሙሉ በሙሉ በግንብ አጥር የተከበበች ነበረች፡ በግንቡ አናት ላይ ሦስት ሰረገሎችን ማሽከርከር እስከምችሉ ድረስ ነበር የግንቡ ውፍረት። እነዚህ እስራኤላውያንም የተበደሩትን፡ ሰይፍና፡ ሌሎች ነገሮች እንጨትና ድንጋይ ይዘው፡ እንዴት ነው ወደዚያ የሚገቡት? እርሱ ግን አሁንም የአብርሃም ዘር ነበር። እግዚአብሔር ራእይ ሰጠው፡ እንዴት ማድረግ እንዳለበት ነገረው፡ እንዲህ አለው፡ "የመለከት ድምጽ አሰማ።" አሜን። ያ ነው በቃ። "ጩኹ፡ ወደ ግድግዳው ተራመዱ፡ ደጆቹ በፊታችሁ ይወድቃሉ።" አሜን! እርሱ የአብርሃም የተመረጠ ዘር ነበር፡ የእግዚአብሔር እውነተኛ አማኝ ነበር። "ደጆቹ በፊታችሁ ይወድቃሉ። ጩኹትና፡ የመለከት ድምጽ ማሰማት ብቻ ነው ያለባችሁ። ማድረግ ያለባችሁ ይህ ብቻ ነው።" ምን ሆነ? የከተማይቱ ደጆች ወደቁ፡ ኢያሱም ከተማዋን ወሰዳት።

59 በኋላም፡ ከዚያ በኋላ፡ ጠላት እየተሸነፈ ወደኋላ ሲሮጥ እንደነበረ እናያለን፡ ፀሐይን እንኳን ባለችበት አቁሟል። በቀደም ጠዋት **እያዋ** በሚል ርዕስ ተናግሬ እንደነበር፡ የጠላቱን ደጅ እስከሚወርሰ ድረስ ፀሐይን አቆማት። አሜን። ጠላቶቹ እንደገና ቢሰባሰቡ፡ ተበታትነው የነበሩት፡ ፀሐይ ሰትጠልቅ፡ አሞራውያን፡ አማሌቃውያንና፡ የመሳሰሉትም፡ ተበታትነው ነበረና፡ እንደገና ቢሰባሰቡ፡ አንድ ቢሆኑ፡ ዳግመኛ ለማሸነፍ ከባድ እንደሚሆንበት ያውቅ ነበር። ጠላቶቹን እንዳያጠፋቸው የሚከለክለው ብቸኛው ነገር፡ ጊዜ ብቻ ነበር፡ ሰለዚህም ጊዜን አቆመ። አሜን! አሜን! ተሰፋውን እንዳይወርሰ የሚያግደው አንድ ነገር ብቻ ነበር፡ ያም ፀሐይ ነበር፡ ተፈጥሮ ራሱ ሊከለክለው ሞከረ፡ ሰለዚህም ተፈጥሮን አቆመ። ለምን? እርሱ የአብርሃም ዘር ነበር። የእግዚአብሔርን ተሰፋ አመነ። ተፈጥሮን አቆመ፡ ደጆቹንም ወረሰ። አዎን፡ ወዳጄ።

60 እነዚህ ታላላቅ ሰዎች፡ ሁሉም ታላላቅ ሰዎች ናቸው። ነገር ግን፡ እያንዳንዳቸው፡ ወደ ሞት ደጅ ሲደርሱ፡ ሁሉም እንደሞቱ ታውቃላችሁ። እያንዳንዳቸው መሞት ነበረባቸው። ታላላቅ ሰዎች ነበሩ፡ "የ—የአንበሶችን አፍ ዘጉ፡ ከእሣትና፡ ከሰይፍ አመለጡ፡" የመሳሰሉትን አደረጉ፡ በዕብራውያን 11 ላይ እንደተነገረን ነው። ከአንዱ ጠላት በቀር፡ የጠላቶቻቸውንም ደጆች ወረሱ፡ እርሱም ሞት ነው። ሞት እያንዳንዳቸውን ዋጠ።

61 ከዚያም አንድ ቀን፡ የአብርሃም የተመረጠ ዘር የሆነው፡ የእግዚአብሔር ልጅ፡ ኢየሱስ ክርስቶስ መጣ፣ በእምነት፡ የአብርሃም ዘር የሆነው። በይስሐቅ በኩል ያልሆነ፡ የሰጋ ዘር ያልሆነ፣ እነዚያ የድርሻቸውን ተወጥተዋል። ነገር ግን በተፈጥሮ ህግ ያልተወለደ አንድ መጣ። በወሲባዊ ፍላጎት ፈጽሞ ያልመጣ አንድ ሰው መጣ። በድንግል በኩል አንድ መጣ። የእግዚአብሔር ልጅ የሆነ፡

የአብርሃም ዘር፡ እንዴት ያለ ታላቅ ሰው ነበር! ሌሎች ዘሮች ሁሉ የተወለዱት በተፈጥሮ ውልደት ነው። ይህ ሰው የተወለደው ከድንግል ነው። ወደ ምድር በመጣ ጊዜ ምን አደረገ? የሰይጣንን ሃይል ሁሉ አሸነፈ። ሁሉንም አሸነፈ።

62 ምን አደረገ? ሄዶ በሽታን አሸነፈ። በእርሱ አጠገብ ምንም በሽታ ሊኖር አይችልም፣ በሽታ ባለበት ቦታ ሁሉ፡ አሸነፈው። ድል ካደረገ በኋላ ምን አደረገ? እንዲህ ሲል፡ ቁልፎቹን ለእኛ ሰጠን፡ አሜን፡ “በምድር የምታሰሩትን ሁሉ፡ በሰማይ አሰረዋለው” አለ። ኦህ! አሜን! ይህ የአብርሃም ንጉሣዊ ዘር ነው፡ ቃል ኪዳኑ ነው። መንፈስ ቅዱስ አሁን በእኛ ውስጥ ነው፡ ቁልፎቹን ይዘናል፡ በበሽታ ላይ ስልጣን ተሰጥቶናል። እርሱ በሽታን አሸነፏል። በሽታ በፊቱ መቆም አይችልም። ተመሳሳይ ነገር እንድናደርግ ዘንድ በሽታን ለማሸነፍ፡ ቁልፍ እንደሰጠን ተናግሯል። “በምድር የምታሰሩት ሁሉ፡ በሰማይ አሰረዋለው።”

63 ደግሞም፡ ፈተናም ጭምር፡ እንደ እኛ በሁሉም መንገድ ተፈተነ። ምን አደረገ? አሸነፈው። ለእኛስ ምንድነው ያለን? “ዲያብሎስን ተቃወሙት፡ ከእናንተም ይሸሻል።” በሽታን ድል አደረገልን። ለእኛ ፈተናን አሸነፈልን፡ ደጆችን ሁሉ ሰበረ፣ ከፈታኙ ቁልፉን ወሰደ፡ ለአማኙ፡ ለአብርሃም ዘር፡ አሳልፎ ሰጠ፡ እንዲህም አለ፡ “እርሱ ቢፈትናችሁ፡ ተቃወሙት፡ እርሱም ከእናንተ ይሸሻል።” ኦህ! ማይ! ተቃወሙት!

64 ሞትንና ሲኦልን አሸንፏል። በሦስተኛው ቀን ተነሣና፡ “አሸንፌአለሁ። እኔ ሕያው ስለሆንኩ፡ እናንተም ሕያዋን ናችሁ” አለ። ኦህ፡ እንዴት ያለ ታላቅ ቃል ኪዳን ነው! ያ ለአብርሃም ዘር ነው። ለጽድቃችን ሲል፡ መቃብሩን አሸነፈ፡ በሦስተኛው ቀን ተነሳ። ከሞት በተነሳ ጊዜ፡ ጽድቃችን እርሱ ነበር። ያ እኛን ምን ያደርገናል? በሽታን አሸንፏል። ሞትን አሸንፏል። ገሃነምን አሸንፏል። መቃብሩን አሸንፏል። ፈተናዎችን አሸንፏል። ኦህ!

65 “አሁን በወደደንና፡ ሕይወቱን ለእኛ በሰጠን በእርሱ ከአሸናፊዎች በላይ ነን፡” የአብርሃም ንጉሣዊ ዘር ሆነናል። በእሱ ውስጥ የነበረውን፡ የእግዚአብሔርን መንፈስ በውስጣችን ካለ፡ ከድል አድራጊዎች በላይ ነን። እያንዳንዱ ደጅ ድል ተደርጎልናል። ማድረግ ያለብን ብቸኛው ነገር መውረስ ብቻ ነው። አስቀድሞ ድል ተደርጓል። በሽታ ድል ተደርጓል። ሞት ድል ተደርጓል። ሲኦል ድል ተደርጓል። መቃብር ድል ተደርጓል። ሁሉም ነገር ድል ተደርጓል፡ ቁልፎቹን፡ በጸጋው እንይዛለን። “በኢየሱስ ክርስቶስ ስም እመጣለሁ፡” ብላችሁ፡ ለመቆለፍ ትፈራላችሁን? “አባቴን በሰሜ ምንም ጠይቁት።” እወደዋለሁ።

66 ሁለት ሺህ ዓመታት ካለፉ በኋላ፡ ሁለት ሺህ ዓመታት፡ አሁንም እርሱ በመካከላችን አለ፡ መጋረጃውን ለሁለት የቀደደው ኃያል ድል አድራጊው፡ ህመማችንን ሁሉ የወሰደ፡ በሽታ ሁሉ፡ ድካማችንን ሁሉ፡ በመስቀል ላይ ተሸክሞ፡ በድል አድራጊነት አሸንፎ፡ ህመማችንና በሽታችንን፡ አስወግዶ፡ ለጽድቃችን ተነሥቶ፡ ከሁለት ሺህ ዓመታት በኋላ፡ ሁሉን ወራሽ በሆኑት በአብርሃም ምርጥ ዘሮች መካከል፡ ራሱን እንደ ሕያው ኢየሱስ ክርስቶስ ለመግለጥ፡ ዛሬ በመካከላችን አለ። ኦህ፡ ማይ! በፈተናዎች ውስጥ፡ በታማኝነት የሚጸኑ፡ የእግዚአብሔርን ተስፋዎችን ይቀበላሉ! ቃሉን

ማመን ከቻላችሁ፡ እናንተም የኢብርሃም ዘሮች ናችሁ ማለት ነው። ወደዚያ የሚትደርሱት፡ በዚህ መንገድ ነው።

67 የቃሉን ፈተና መፈተን ካልቻላችሁ፡ ከተጠራጠራችሁት፡ ትንሽ ከተጠራጠራችሁት፡ ማመን ካልቻላችሁ፡ የሆነ ነገር አለ ወይም ሌላ ነገር አለ፡ ማመን ካልቻላችሁ፡ ወደ ጸሎት መሰመር እንዳትመጡ። የእግዚአብሔር ቃል እውነት መሆኑን ለማመን በቂ ጸጋ እስክታገኙ ድረስ፡ በመሰዊያ ላይ ሰለ ፈውስ በመጸለይ ራሴን ማታለል አልፈልግም።

68 እንዴ ያንን የእምነት ማጣት መጋረጃ ካለፋችሁ፡ የገሃነም፡ የመቃብርና፡ የሰኦል ቁልፎች፡ በእጃቻችሁ ነው ማለት ነው፡ ምክንያቱም ያሸነፈላችሁ አሸናፊ አላችሁ። ከዚያም ዕብራውያን 13፡8፣ እንዲህ ይለናል፡ "ኢየሱስ ክርስቶስ ትናንትም፡ ዛሬም፡ ለዘለዓለምም ያው ነው።" እንዴት ማድረግ እንችላለን?

69 በዛሬው ጊዜ ሰዎች፡ "ኦህ፡ ደህና፡ እንነግራችኋለን፡ እሱ እ—እንደዛ ነው፡ እሱ እንዲህ ነው" ይላሉ።

"እርሱ ያው ነው፡" ይላል መጽሐፍ ቅዱስ።

"አዎ፡ እሺ፡ ያኔ እንደምሰራው ዛሬ አይሰራማ" ይላሉ።

70 ቃሉ እንደተረጋገጠ ሰናይ፡ አሁን እናያለን። ምን ያደርጋል? ያንን ሲያደርግ እንደገና እንዲወሰኑ ሃላፊነቱን በላያቸው ላይ ያደርጋል። አሜን።

71 የአብርሃም እውነተኛ ዘር ያምናል። ያውቃሉ። ዛሬ ማታ፡ በሎጥ ዘመን፡ ከአብርሃም ጋር ተገናኝቶ ያንን ተአምር እንዳደረገ፡ ለሣራ በጀርባ የተናገረችውን የልቧን አውቆ እንደተናገረ ዛሬም እንደዛው ሆኖ በመካከላችን አለ። ኢየሱስ፡ የአብርሃም የተመረጠ ዘር፡ ቤተክርስቲያን ከመምጣቱ በፊት ተመሳሳይ ነገር እንደምትመለከት ቃል ገብቷል። ምንድነው? መሆን አለበት። እግዚአብሔር ቃል ገብቷል። ኢየሱስ ክርስቶስ ይህን አረጋግጦ እንደሚሆን ተናግሯል፡ ዛሬ፡ ከሁለት ሺህ ዓመታት በኋላ፡ እርሱን በመካከላችን እናየዋለን፡ አሁንም ኃያል ድል አድራጊ ነው! ሞትን፡ ሲኦልን፡ መቃብርን፡ ሁሉንም ዐጉል እምነቶችን አሸንፏል፣ ቃሉን... ? ... እሷን። አዎን።

72 እንዲህ ብሏል፡ "በእኔ ብትኖሩ፡ ቃሌም በእናንተ ቢኖር፡ የምትወዱትን ሁሉ ለምኑ ይሰጣችኋል" ብሏል። ምን ነበር? በልባችሁ ውስጥ ያለው፡ ቃል፡ ክርስቶስ ነው። "በእኔ ብትኖሩ፡ ቃሌም በእናንተ ቢኖር፡ ሁሉንም አሸንፋችኋል ምክንያቱም እኔ ሰለ እናንተ አሸንፌዋለሁና። በእኔ ብትኖሩ፡ እኔን መረዳት ከቻላችሁ፡ በእኔ ብትኖሩ። በእኔ የሚያምን፡ እኔን ይቀበላል፣ አስመሣይ-እምነት ብቻ ሳይሆን፡ ሊቀበል ይችላል። ቃሌን የሚሰማ፡ ቃሌንም የሚረዳ፡ የላከኝንም የሚያምን፡ የዘላለም ሕይወት አለው፣ ወደ ፈተናም አይመጣም፡ ወይም ወደ ኩነን አይመጣም፡ ነገር ግን ከሞት ወደ ሕይወት ተሻግሯል።" ይሄው፡ እርሱ ታላቅ አሸናፊ ነው!

73 እርሱ ዛሬም ያው ነው፡ ትናንትና፡ ዛሬና፡ ለዘለዓለም ያው ነው። ከባቢሎን፡ ከሰዶም ከዓለም የተጠራውና የተለየው የአብርሃም ዘር ፊት፡ በመገኘት፡ የገባውን ቃል፡ በትክክል እንደሚፈፅም፡ እያሳየ ነው። ከሁለት ሺህ ዓመታት በኋላ፡ ዛሬ ማታ፡ በመካከላችን ቆሟል፡ ያ ኃያል ድል አድራጊ፡ የእግዚአብሔር ቃል በልብ ውስጥ ያለውን ሃሳብና፡ ዓላማ መረዳት የሚችል በመካከላችን አለ።

ምንድነው? “ዘርህ የጠላትን ደጅ ይወርሳል።” ምንድነው? የአብርሃም ዘር ነው፡ የተመረጠ ዘር ነው፡ ቃሉን ያምናል። ቃሉ ደግሞ—ቃሉ እግዚአብሔር ነው።

74 አሁን ይህንን ሰናይ፡ ከጥንቱ ግጥም ጋር፡ አብረን ልንጮህ እንችላለን፡

ሕያው ሆኖ፡ ወደደኝ፣ እየሞተ፡ አዳነኝ፣
ተቀብሮ፡ ሐጢአቴን አራቀ፣
ሲነሳ፡ ለዘላለም በነጻ አጸደቀኝ፡
አንድ ቀን ይመጣል—ኦህ፡ በክቡር ቀን!

75 አንድ ሰው፡ “ልጄ ሆይ፡ አርጅተሃል” አለኝ። ምንም ማድረግ አልችልም።

76 እኔ ከልጅነቴ ጀምሮ ኖሬአለሁ፡ ያገኘሁት ብቸኛ ስኬት የኢየሱስ ክርስቶስን መምጣት ማየት ነው። ሕይወቴን ለዚህ ዓላማ ሰጥቻለሁ። አሁንም እንደ ሽማግሌ፡ በወንጌል መድረክ ላይ ነኝ፡ ተመሳሳይ ታሪክ አምናለሁ፡ ማሰብ የምችለው ትልቁ ነገር ኢየሱስ ክርስቶስን የራሱ የሆኑትን ለመቀበል ከሰማይ ሲመጣ ማየት ነው። እግዚአብሔር ሆይ፡ እንግዲያውስ... መዘመራችን አያስደንቅማ፡

ሁሉም የኢየሱስን ኃያል ስም ያወድሱ!
መላእክትም ይሰገዱ፣
የክብር ዘውድ ይምጣ፡
የሁሉም ጌታ ዘውዱን ያድርግ።

77 ለምን? እርሱ ኃያል ድል አድራጊ ነው። በእርሱ ውስጥ ከሆንክ፡ በቃሉ ውስጥ ነህ። “በእኔ ብትኖሩ፡ የምትወዱትን ሁሉ ለምኑ፡” ብሏል። “የምትወዱትን” ሁሉም ደጆች ድል ተደርገዋል። ከዚያም እንዲህ ማለት እንችላለን፥

የመጽሐፉ ተስፋ ሁሉ የእኔ ነውና፡
ምዕራፍ ሁሉ፡ ቁጥር ሁሉ፡ መስመር ሁሉ የእኔ ነውና።
በመለኮታዊው ቃሉ ላይ እታመናለሁ፡
የመጽሐፉ ተስፋ ሁሉ የእኔ ነውና፡

78 ወዳጆቼ፡ ይህ ምን ማለት እንደሆነ ተገንዝባችኋል? እግዚአብሔር ለአብርሃም የገባው ቃል ኪዳን ሁሉ፡ በነቢያት የተነገረው ቃል ሁሉ፡ ኢየሱስ ክርስቶስ ለዚህ ቀን የገባው ቃል ሁሉ፡ እርሱ ይህን ለማረጋገጥና እርሱ ለዘላለም ህያው ሆኖ እንደሚኖር ለማሳየት እዚህ አለ። “ዘርህ የጠላቶችን ደጅ ይወርሳል።”

79 የሞት ሰዓት ስትደርስ። “ያ ምንድነው፡” ማለት ትችላላችሁ? ጳውሎስ የተናገረውን ርስት አሁንም አላችሁ፡ “ሲኦል ሆይ፡ ድል መንሳትህ የታለ? ሞት ሆይ፡ መውጊያህ ወዴት ነው? ነገር ግን በኃይለኛው ድል አድራጊ በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል፡ ድልን ለሚሰጠን፡ ለእግዚአብሔር ምስጋና ይሁን።” ኦህ!

መላእክትም ይሰገዱ፡
የክብር ዘውድ ይምጣ፡
የሁሉ ጌታ የሆነውን እንግሱት።

80 ዛሬ ማታ፡ ከሁለት ሺህ ዓመታት በኋላ፡ አሁንም፡ ኃያል ድል አድራጊውን፡ እርሱን ለማየት ቆመናል እግዚአብሔር ከቃል ኪዳኑ የሚለየንን መጋረጃ የቀደደውን እርሱን ለማየት ቆመናል፡ በእርሱም ከአሸናፊዎች በላይ ነን። እንጸልይ።

81 በሰማይ የምትኖር አባት ሆይ፡ ዛሬ ማታ፡ በመንፈስ ቅዱስ ፊት፡ በአብርሃም ዘር፡ በተመረጠ ዘር እንደሚመጣ ቃል በተገባለት፡ በመንፈስ መልክ በታላቁ የኢየሱስ ክርስቶስ አካል ፊት ቆመን፡ አምላካችን ሆይ፡ በዚህ ውስጥ፡ አንተን የማያውቅ፡ ወንድ ወይም ሴት፡ ወንድ ልጅ ወይም ሴት ልጅ ቢኖሩ፡ እንጸልያለን፡ ስለ እግዚአብሔር ቃል፡ እውነት ይሁን አይሁን፡ በአእምሯቸው ውስጥ ጥርጣሬዎች አላቸው፡ ቃል የገባኸው፡ ኦህ ታላቁ አምላካችን ሆይ፡ ዛሬ ማታ ና! ጌታ ሆይ፡ አንድ ታላቅ ቃል ገብተሃል፡ ያንን ቃል ማክበር ትችላለህ፡ እንዲህ ብለሃል፡ "በእኔ የሚያምን፡ እኔ የማደርገውን ሥራ ደግሞ ያደርጋል፣ ከዚህም የሚበልጥ ያደርጋል፡ ወደ አብ እሄዳለሁና።" አባታችን እግዚአብሔር ሆይ፡ ቃልህን እንድታረጋግጥልን እንጸልያለን።

82 ዛሬ ማታ ብዙ የታመሙ፡ የአብርሃም ልጆች እዚህ አሉ። ኦህ፡ ዲያቢሎስ ደጁን ዘግቶባው፣ በውስጥ አስቀምጠው፡ ዘግቷል፡ እንዲህም አለ፡ "አሁን መሞት አለብህ፣ የልብ ችግር አለብህ። **ይህንን፡ ያንን**፡ ወይም **ሌላው** አለብህ፡ መሞት አለብህ።"

83 እግዚአብሔር ሆይ፡ የወንጌሉ፡ የኢዮቤልዩ ቀንደ መለከት፡ ዛሬ ማታ ይነፋ፡ በዚህም እያንዳንዱ ባሪያ ነጻ ይውጣ! ኢየሱስ ክርስቶስ እነዚያን በሮች አሸንፏል። ቁልፎቹን በእጆችን እንይዛለን። ኦህ! "በስሜ አጋንንትን ያወጣሉ። በስሜ አብን ብትለምኑ፡ እኔ አደርገዋለሁ። በእኔ የሚያምን፡ እኔ የማደርገውን ሥራ እርሱ ደግሞ ያደርጋል። የእግዚአብሔር ቃል ሁለት-አፍ ካለው ሰይፍ ይልቅ የተሳለ ነው፡ ነፍስንና አጥንትንም ይቈርጣል፡ የልብንም አሳብ ይመረምራል።"

84 "በኖኅ ዘመን እንደነበረው ሁሉ፡ የሰው ልጅ በሚመጣበት ጊዜም እንዲሁ ይሆናል፡ ምክንያቱም ሰዎች ይበሉና፡ ይጠጡ፡ ያገቡና፡ ይጋቡም ነበር፡ ታላላቅ የግንባታ ፕሮጀክቶችን ሲያደርጉ ነበር።" ዓለምንም እንመለከታለን፡ "ምልክቶች ይሆናሉ፡ አስፈሪ ምልክቶች በሰማይ ላይ (ይህ የሚበሩ ሳውሰሪስ ናቸው)፡ የመሬት መንቀጥቀጦች በተለያዩ ቦታዎች፡ የባሕሩ ጩኸት (የማዕበል ሞገዶች)፡ የሰዎች ልብ እየደከመ (ፍርሃት)፡ በሃገራት መካከል ጭንቀት፡ በጊዜ ግራ መጋባት እነዚህ ምልክቶች ይታያሉ።"

85 "በሎጥ ዘመን እንደነበረው፡ የሰው ልጅ መምጣትም እንዲሁ ይሆናል።" አምላክ ሆይ፡ ዛሬ ማታ መጥተህ ቃልህን ፈጽም፡ ዛሬ ማታ መጥተህ የአብርሃም ልጆችን እምነት አክብር። በኢየሱስ ክርስቶስ ስም እንጠይቃለን። አሜን።

86 ጌታ አብዝቶ፡ ይባርካችሁ። በዚህ ጊዜ የመሠዊያው ጥሪ አላደርግም። ለእኛነት ልተወው ነው። እንደማስበው፡ ብዙ ጊዜ፡ መሠዊያ ጥሪ... አብሬያቸው አምናለሁ። "የተቀበሉት ሁሉ ግን፡ ተጠመቁ" ይላል። ያ ነው በቃ፡ "የተቀበሉት ሁሉ።" ለታመሙ ሰዎች እንጸልያለን።

87 እዚህ ሌሊቱን ሙሉ መናገር እችላለሁ። እናንተ ደስ የሚትሉ ህዝቦች ናችሁ። ነገር ግን እኔ ከተናገርኩ ሰው ነው የተናገረው፡ ነገር ግን የእርሱን ቃል

ከተናገርኩ፡ የእኔ ቃል አይደለም፡ የእርሱ ቃል ነው። አንድ ነገር ከተናገርኩና፡ እግዚአብሔር የማይደግፈው ከሆነ፡ ያ የእኔ ቃል ነበር ማለት ነው። ቃሉን ከተናገርኩ፡ ይደግፈዋል፡ ኃጢአተኛ የሆነ ወንድ ወይም ሴት፡ ወንድ ልጅ ወይስ ሴት ልጅ፡ ማነው አይደለም የሚለው?

88 ኢየሱስ፡ እነዚህን ነገሮች ሲያደርግ ተብሏል፡ እንዲህ አሉት፡ "ይህ ሰው ሟርተኛ ነው። ጋኔን አለበት!" ሟርተኛ፡ ሟርተ-ኛነት የዲያብሎስ እንደሆነ ሁሉም ሰው ያውቃል። እንዲህ አለ፡ "ሟርተኛ ነው" አለ። ሟርተኛ ወንጌልን ሲሰብክ አይታችሁ ታውቃላችሁን? ሟርተኛ አጋንንትን ሲያሰወጣ አይታችሁ ታውቃላችሁ? አይ፡ በጭራሽ፡ አያደርጉትም።

89 እንዲህ አለ፡ "አሁን፡ እኔ የሰው ልጅ ለዚህ ይቅር እላችኋለሁ" አለ። ነገር ግን መንፈስ ቅዱስ ሲመጣ፡ በእርሱ ላይ የሚናገር ሁሉ በዚህ ዓለም ወይም በሚመጣው ዓለም ይቅር አይባልም፡ ምክንያቱም የእግዚአብሔርን ሥራ ርኩስ መንፈስ ብሎ ስለጠራ ነው።"

90 እግዚአብሔር፡ ዛሬ ማታ ራራልን፡ እግዚአብሔር እንዲወርድና ይህን ቃል በፊታችሁ እንዲያረጋግጥ እጸልያለሁ።

91 ወንድሜ፡ እኅቴ፡ ይህ ነፍሴ ነው። ከእግዚአብሔር ጋር መገናኘት አለብኝ። ስለምነግራችሁ ነገር ተጠያቂው እኔ ነኝ። እግዚአብሔርም ተጠያቂ ያደርገኛል። በትክክል። ነፍሴን ለገሃነም እንደምጥል እያወኩ እዚህ ቆሜ እነዚህን ነገሮች መናገሬ ምን ይጠቅመኛል?

92 "ለሰው ትክክለኛ መስሎ የሚታየው መንገድ አለ፡ ፍጻሜው ግን የሞት መንገድ ነው።" እግዚአብሔር ተርጓሚ አያስፈልገውም። እንደነገርኳችሁ፡ ቃሉን ራሱ ይተረጉመዋል።

93 "የአብርሃም ዘር የጠላት ደጅ ይወርሳል።" ይህን ታምናላችሁ?

94 መፈወስ ብችል፡ እፈውሳችሁ ነበር። ክርስቶስ አስቀድሞ ፈውሷችኋል። አንድ ነገር፡ ቁልፉ በእጃችሁ ውስጥ ነው። ፈውስ እንዲታገኙ የሚያደርግ፡ ያ ቁልፍ እምነታችሁ ነው። ዛሬ ማታ፡ ክፈቱት፡ አትከፍቱም? እርሱ በመካከላችን በሚመጣበት ጊዜ፡ ያ ሁሉን በሽታ ያሸነፈ ኃያል ድል አድራጊ፡ እዚህ መጥቶ ሁሉንም እንደጨረሰው ያሳያችኋል፡ አሁንም ቃል ነውና። "ቃሉ በልብ ውስጥ ያሉትን ሃሳቦች ይመረምራል።"

95 የትኛው የጸሎት ካርድ? ቢ፡ አንድ እስከ... በቀደም ምሽት፡ ከየት ነው የጀመርነው? [አንድ ሰው እንዲህ አለ፡ "አንድ።"—አርታዒ።] ከሃምሳ እንጀምር። የጸሎት ካርድ ቢ፡ ኀምሳ የያዘ? እጅህን አንሳ። የጸሎት ካርድ ቢ። ባለፈው ምሽት፡ ከአንድ ነው የጀመርነው፡ አሁን ዛሬ ማታ፡ ደግሞ ከሃምሳ እንጀምራለን።

96 ቢ፡ ቢ፡ ኀምሳ ያለው ማን ነው? እጃችሁን አንሡ። የጸሎት ካርድ ቢ፡ ኀምሳ። እዚህ የለም ማለት ነው? ይዘሃል? እሺ፡ ቢ፡ ኀምሳ። ቢ፡ ኀምሳ-አንድ፡ የያዘው ማን ነው? ቢ፡ ኀምሳ-አንድ፡ እሺ። ቢ፡ ኀምሳ-ሁለት፡ ቢ፡ ኀምሳ-ሁለት የያዘው ማነው? እሺ፡ ይዘሃል። ቢ፡ ኀምሳ-ሦስት፡ ኀምሳ-አራት፡ ወደዚህ ኑ። ኀምሳ-አራት፡ ኀምሳ-አምስት።

97 ልጄ እኔ ከመምጣቴ በፊት፡ ወደዚህ ወርዶ፡ ካርዶችን በታትኖአቸዋል። እንዴት እንደሆኑ ተመልከቱ፡ አንዱ **እዚህ** አንዱ **እዚያ**? እነሱ እያውቁትም። **እዚህ** ረድፍ መጥታችሁ አንድ ማግኘት ትችላላችሁ፡ ቀጣዩ ላይ አስር ያገኛል፡ ሌላኛው ደግሞ ሃያ-አምስት ያገኛል። የት እንዳለ አናውቅም፡ ነገር ግን፡ የትም ይሁኑ የት ችግር የለውም።

98 አሁን ስንት ነው የጠራነው? አምስት፡ አራት? ቢ፡ ኀምሳ። ቢ፡ ኀምሳ ነበር፡ አይደል? [አንድ ሰው እንዲህ አለ፡ "አዎን።"—አርታዒ።] ቢ፡ ኀምሳ እስከ ኀምሳ-አምስት። ኀምሳ-ስድስት፡ ኀምሳ-ሰባት፡ ኀምሳ-ስምንት፡ ኀምሳ-ዘጠኝ፡ ስድሳ። አሁን እስቲ እንመልከት፡ አንድ፡ ሁለት... ቢሊ፡ ቁጥራቸው፡ ሰ... ሰልሳ፡ ሰባ፡ እስቲ፡ ይቁሙ መጀመሪያ። ቢ፡ ኀምሳ እስከ ሰባ፡ ሰባ-አምስት። ፈቃደኛ ከሆንክ፡ ቁጠራችሁ፡ ወንድም ሮይ፡ እኔ ከጉባኤ ጋር እየተናጋገርኩ እቆያለሁ።

99 በዚህ አቅጣጫ ስትመለከቱ ስንት ሰዎች አሉ፡ የጸሎት ካርድ አላገኛችሁም?

100 አስታውሱ፡ ኢየሱስ እንዲህ ብሏል፡ "እኔ የማደርገውን እናንተም ደግሞ ታደርጋላችሁ።" ይህ እውነት ነው? እውነት ነው። ይህን ታምናላችሁ? የአብርሃም ዘር እንዲህ ብሏልና።

101 መጽሐፍ ቅዱስ፡ እንዲህ ይላል፡ "እርሱ ሊቀ ካህን ነው።" ዕብራውያን፡ ምዕራፍ 4፡ "እርሱ በደካማነታችን ስሜት ሊነካ የሚችል ሊቀ ካህን ነው።" ይህን ታምናላችሁ? እሱ ትናንት፡ ዛሬና፡ ለዘላለም ያው ከሆነ፡ እንዴት ያደርገዋል?

102 በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ፡ አንዲት ምስኪን ሴት ነበረች፡ የሚናገረውን እያስተዋላችሁ። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ፡ አንዲት ምስኪን ሴት ነበረች፡ ምናልባትም ጸሎት አልነበራትም፣ ነገር ግን በልቧ እንዲህ አለች፡ "ያንን ሰው መንካት ከቻልኩ፡ እምነዋለው።" ያላትን በሙሉ ለዶክ-... ለዶክተሮች ከፍላ፡ ጨርሳለች። ሊረዱዋት አልቻሉም። ህመሟ በጣም ከባድ ነበር። ሊረዱዋት አልቻሉም። ነገር ግን እግዚአብሔር እንደሚረዳት አመነች። የልብሱንም ጫፍ፡ ነካች።

103 እንዲህ አለ፡ "ሃይል ከእኔ እንደወጣ አስተዋልኩ።" ይህ እውነት ነው?

104 ዛሬ ማታ፡ ያው ነው ብላችሁ ታምናላችሁን? እዚህ አለ ብላችሁ ታምናላችሁን? ሙታን እንዳስነሳ ሰንቶቻችሁ ታምናላችሁ? አሁን እርሱ ሙታን እንዳስነሳ እንዴት ማረጋገጥ ትችላላችሁ?

105 በቅርብ ጊዜ፡ አንድ ታዋቂ የባፕቲስት ሰው ወደ እኔ መጥቶ፡ እንዲህ አለ፡ "ወንድም ብራንሃም፡ በአንድ ወቅት፡ አንድ መሐመዳዊ ይህን በተናገረ ጊዜ፡ ተ—ተሸንፌ ነበር። እንዲህ አለ፡ 'እርሱ ከሞት ካስነሳ፡ ተመሳሳይ ነገር እንደሚያደርግ ቃል ገብቶልናል። እስቲ ይህን ሲያደርግ እንመልከት።"' አያችሁ፡ ይህን አላደረገም ብለው ያምናሉ።

106 ነገር ግን እንደሚያደርገው እናምናለን። ከሙታን እንዳስነሳ እናምናለን። በዓለም ላይ ፈጣሪያቸው ሕያው እንደሆነ ሊያረጋግጥ የሚችል ሌላ ሃይማኖት የለም፡ ክርስትና ብቻ ነው። እግዚአብሔር ሊያረጋግጠው የሚችለው ብቸኛው

መንገድ፡ በእሱ በሚያምኑት በኩል ነው፡ ምክንያቱም እግዚአብሔር ቃሉን የሚፈጽምበት ብቸኛው መንገድ፡ በእሱ በሚያምኑት ነው።

107 አሁን በዚህ ትንሽ የጸሎት መስመር ውስጥ እየተሰለፉ ሳሉ፡ ስንት እንደምናገኝ አላውቅም፡ እያንዳንዳችሁ፡ ቦታችሁን እንዲትይዙ፡ መቀመጫችሁን እንዲትይዙ፡ እንዳትንቀሳቀሱ እፈልጋለሁ፡ ወደዚህ ተመልከቱና፡ እንዲህ በሉ፡ “ጌታ ኢየሱስ፡ እምናለሁ።”

108 አስታውሱ፡ እንዲህ ብሎ ነገረኝ፡ “ሰዎች እንዲያምኑህ ካደረክ፣ በምትጸልይበት ጊዜ ቅን ሁን።” “ይህ በአገሪቱ ውስጥ፡ በሁሉም ቦታ፡ ለአሥራ አምስት ዓመታት፡ አንድ ጊዜም አልወደቀም። ሊወድቅ አይችልም።

109 እግዚአብሔር፡ እግዚአብሔር ሊያደርገው የማይችለው አንድ ነገር አለ፡ ያም መውደቅ ነው። ቃሉን ይጠብቃል። ይህን እምናለሁ። እኔ አሁን እዚህ መቆሜን ከማምነው አብዝቼ... ይሄን እምናለሁ፣ በዚህ ሕንጻ ውስጥ መሆኔን ከማመን በላይ፡ ይህ ቅዠት ሊሆን ይችላል፡ ሕልም ሊሆን ይችላል። በነፍሴ፡ የእግዚአብሔር ልጅ ኢየሱስ ክርስቶስ ሕያው መሆኑን አውቃለሁ። የአብርሃም ዘር በመሆናችሁ፡ በክርስቶስ ሙታን በመሆናችሁ፡ የአብርሃም ዘር ናችሁ።

110 አሁን እዚህ ላይ አንዳንድ መሃረብ አሏቸው። ይህንን የሚያምኑ፡ ሰዎች ትልቅ ስኬት አግኝተዋል። አሁን ራሳችንን ዝቅ እናድርግና፡ እነሱ እየተዘጋጁ ሳሉ፡ ስለ እነዚህ እንጸልይ።

111 የሰማይ አባት ሆይ፡ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ተምረናል፡ የተናገርከው እያንዳንዱ ቃል እውነት ነው ብለው የሚያምኑ ሰዎች እዚህ አሉ። ጌታ ሆይ፡ አንዳንድ ጊዜ ይደናቀፋሉና፡ ቁልፍ ይዘው በቁልፍ ቀዳዳው ይጋጫሉ፡ ያመልጣቸዋል፡ ይቸገራሉ፡ ቁልፉ ግን እንዳለ ያምናሉ። ትግላቸውን ይቀጥሉ፡ እዚያ ሰላለ፡ ያገኙታልና። ቁልፉ ትክክለኛው ቁልፍ ነው፡ “ለሚያምን፡ ሁሉ ይቻላል።” መዝሙሩ አሁን እየተዘመረ ሳለ፡ ወይም እየተጫወተ ሳለ።

112 በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ እንዲህ ይላል፡ “ጳውሎስ መሃረቦችንና መጎናጸፊያዎችን ወሰዶ፡ ለታመሙና ለተጎዱት ይልክላቸው ነበር፡ ርኩሳን መናፍስትም ከሕዝቡ ይወጡ ነበር፡ እነርሱም ይፈወሱ ነበር።”

113 አሁን፡ ጌታ ሆይ፡ ቅዱስ ጳውሎስ ከአንተ ጋር እንደሆነ እናውቃለን። ነገር ግን፡ እርሱ አልነበረም፣ አንተ ነህ፡ ጌታ ሆይ፡ ክርስቶስ በእርሱ ውስጥ ነበር። “እኔ አይደለሁም፡ ክርስቶስ ግን በእኔ ውስጥ ይኖራል፡” አለ።

114 አሁን ለዚህ ትውልድ፡ ዛሬም፡ ትናንትም እንደነበርከው ሁሉ፡ አንተ ክርስቶስ ነህ። በእነዚህ መሃረቦች ላይ ስጸልይ፡ ስነካቸው፡ እያንዳንዱን ጠላት እንድታሸንፍ እጸልያለሁ። ጠላት እንደተሸነፈ እንዲያውቁ፡ እምነት ስጣቸው።

115 አንድ ጊዜ፡ ቅድም እንደተናገርነው፡ እስራኤል በግዳጅ ላይ ሆነው፡ ወደ ተስፋይቱ ምድር ሲጓዙ፡ ቀይ ባሕር ከፊታቸው ከለከላቸው። አንድ ጸሐፊ እንዲህ አለ፡ “እግዚአብሔርም በቍጣ ዓይኖች በዚያ እሳት አምድ፡ ወደ ታች ተመለከተ፡ ባሕሩም ፈራና በሮቹን ከፈተ፡ እነርሱም ተሻገሩ።”

116 ዛሬ ማታ፡ በኢየሱስ ክርስቶስ ደም አማካኝነት፡ ወደ ታች ተመልከት። እነዚህ ጨርቆች በታመሙ ሰዎች ላይ፡ ሲጫኑ፡ ዛሬ ማታ፡ ለእነሱ ይህንን

የእምነት ጸሎት ስንጸልይ፡ ጠላት እምነታችንን ይየው። እያንዳንዱ ሰው ነጻ ይውጣ፡ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም። አሜን።

117 አሁን ሙሉ ትኩረታችሁን እጠይቃለሁ። እዚህ ላይ ማይክሮፎኑ ላይ ያለ ማንኛውም ሰው፡ ድምፁን ከፍ ማድረግ ይችላል። ምክንያቱም፡ መንፈስ ቅዱስ ይህንን ቢያደርግ... እሱ ያደርጋል አልልም።

118 አሁን ማንም ወደዚህ መጥቶ የታመሙትን የመፈወስ ኃይል አለኝ ብሎ ቢነግራችሁ፡ አትመኑት። ኃይሉ ሁሉ በክርስቶስ ውስጥ ነው። እሱ አሸናፊ ነው፡ እኔና እናንተ አይደለንም። እሱ ያደረገውን ብቻ እንቀበላለን። ማንም ሰው የማዳን ወይም የመፈወስ ኃይል የለውም።

119 በዓለም ላይ ያለ እያንዳንዱ ሰው፡ ዋጋው ቀድሞውኑ ተከፍሏል። መሰፈርቱ ተከፍሏል። እንዴት ነበር? "እርሱ ግን ስለ መተላለፋችን ቈሰለ፡ በእርሱ ቍስል እኛ ተፈወስን።" ፈ—ፈውሳችሁ ተከፍሏል። ደንነታችሁ ተከፍሏል። መጥታችሁ ለመውሰድ፡ እምነት አላችሁ? ያ ነው በቃ። የአብርሃም ዘር ከሆናችሁ፡ አላችሁ። እግዚአብሔር ቃል ገብቶላችኋል። በውስጣችሁ የሆነ ነገር አለ ይህም እዚያ እንዳለ ይናገራል፡ አለ።

120 አሁን ሰጦታ ምንድን ነው? ሄዶ ሰዎችን ለመፈወስ ነው ሰጦታ? አይ። ሰጦታ ራስህን ከመንገድ ለማውጣት ነው፡ ስለዚህም እግዚአብሔር ሊጠቀምብህ ይችላል።

121 አሁን ቃል ገብቷል፡ ኢየሱስ እንደተናገረው ከሆነ፡ የመጨረሻው ምልክት፡ "ገና ከመቃጠሉ በፊት፡ በሰዶም ዘመን እንደነበረው ነው።" ሌሎች ነገሮች ከመከሰታቸው በፊት፡ ወንጌል በሎጥ እንዲሁም በሌሎች፡ ተሰበከ፣ ያ አይደል። ነገር ግን ከመቃጠሉ በፊት፡ እግዚአብሔር በሰው መልክ ወርዶ፡ ከተመረጠችው ቤተክርስቲያን፡ ከአብርሃምና የቃል ኪዳኑ ባለቤት ከሆኑት ወገኖቹ ጋር ተቀመጠ።

122 አሁን አስታውሱ፡ የአብርሃም ዘር ብቻ ይህንን ይቀበላል። "ከጥቂት ጊዜ በኋላ ዓለም ከእንግዲህ አያየኝም፡" አለ ኢየሱስ። "እናንተ ግን ታዩኛላችሁ፡ ምክንያቱም፡ እኔ እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ፡ በውስጣችሁ እሆናለሁ።"

123 ዳግመኛ ከመመለሱ በፊት ግን፡ እንዲህ በማለት ቃል ገብቷል፡ "በሰዶም እንደነበረው፡" የሰዶምን ነገር ተመልከቱ፡ የተመረጠችውን ቤተክርስቲያንን ተመልከቱ፡ "የሰው ልጅ በሚመጣበት ጊዜም እንዲሁ ይሆናል፡" ብሏል። እግዚአብሔር በሰው መልክ ተገለጠ፡ ወደ ድንኳኑ ጀርባውን አዙሮ፡ በድንኳኑ ውስጥ ሣራ ያደረገችውን ተናገረ። ያ እውነት መሆኑን የምታውቁ፡ እጆቻችሁን አንሡ። በትክክል። አሁን እርሱ ቃል ገብቷል። በመጨረሻው ዘመን ላይ ነን። አሁን አስታውሱ፡ የሆነው የመጨረሻው ነገር ያ ነበር፣ የአሕዛብ ዓለም ተቃጠለ፡ ሰዶምና፡ የተሰፋው ልጅ ወደ ቦታው መጣ። የእግዚአብሔርን ልጅ፡ የተሰፋውን ልጅ እንጠባበቃለን።

124 ይሄው እዚህ ነን። እግዚአብሔር ዓይኖቻችሁን ይከፍትላችሁ። ሌላ ምን ማለት እንዳለብኝ አላውቅም። እግዚአብሔር ዓይኖቻችሁን ይከፍትላችሁ።

125 አሁን የሰማይ አባት ሆይ፡ እኔ ምንም ማድረግ የማይችል፡ የተቀረጸና፡ እዚህ የተቀመጠ የሸክላ ዕቃ ብቻ ነኝ። አምላክ ሆይ፡ አቤቱ፡ ዛሬ ማታ፡ ጸጋህና

መገኘትህ ይሁንልኝ፡ ይህም እዚህ ያገኘሃቸውን እነዚህን የሸክላ ስብርባሪዎች መጠቀም ትችል ዘንድ ነው። ጌታ ሆይ፡ እነዚያ፡ ወደ ዘለዓለማዊ ሕይወት የጠራሃቸው፡ ምናልባትም ገና ያልተቀበሉትን፡ ተስፋዎችን ማየት ይሁንላቸው። ይህ ለሌላ ቀን እንደሆነ ሊማሩ ይችሉ ይሆናል፡ ነገር ግን እዚህ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ይገኛል። ጌታ ሆይ፡ አረጋግጥልን። ያ የራስህ ትርጓሜ ነው። ከዚህ በላይ አያስፈልግም። ካደረከው፡ ከዚያም ቃልህ እውነት መሆኑን ያያሉ። ስጠን፡ አባት ሆይ። ራሳችንን አሳልፈን ላንተ እንሰጣለን።

126 ጌታ ሆይ፡ በዚህ ውስጥ ያለ እያንዳንዱ ሰው፡ ዛሬ ማታ፡ እምነቱን ይጠቀም። በኢየሱስ ክርስቶስ አማካኝነት፡ የአብርሃም ዘር የሆነ እያንዳንዱ ሰው፡ ዛሬ ማታ፡ እምነት ይኑረው፡ መገኘትህንም ይቀበል። ምስጋናችንን እናቀርብልሃለን። አሜን።

127 አሁን፡ ይ-... ይህ እንግዳ ነገር ነው። አሁን እንድትረዱኝ እፈልጋለሁ፡ ጸልይሉኝ። በጸጥታ ተቀመጡ፡ አትንቀሳቀሱ። ዝም ብላችሁ ተቀመጡ፡ ጸልዩ።

128 አሁን፡ እያችሁ፡ ከሰብከት እየተለወጠ ነው፡ የእግዚአብሔር መንፈስ ሙሉ በሙሉ ወደ ሌላ ዳይመንሽን እንዲወስድህ እራስህን በዚህ መንገድ አሳልፈህ ትሰጣለህ።

129 አሁን እዚህ ይህች ወጣት... ትንሽ ወደዚህ ተጠጊ፡ እመቤት። መ... መልካም፡ ስለዚህ ከዚህ ማይክሮፎን ፈቀቅ አልልም። እያችሁ፡ ምን እንደሚሆን አላውቅም፡ እያችሁ፡ ከዚያም አንዳንድ ጊዜ፡ ታውቃላችሁ... የማውቀው ብቸኛው መንገድ፡ በ—በማይክ ላይ መሆኑን ነው፡ እያችሁ፡ እነርሱ እዚያ ለመያዝ እየሞከሩ ነው፡ እኔ ግን አላውቅም።

130 አሁን እኛ እርስ በርሳችን እንግዶች ናቸው። አላውቅሽም፡ በሕይወቴ ውስጥ አይቼሽ አላውቅም። ነገር ግን ከእኔ በጣም በእድሜ ታንሽያለሽ። ምናልባት በማይሎች ልዩነት ተወልደናል፡ በዓመታት ልዩነት። ለመጀመሪያ ጊዜ የተገናኘነው ዛሬ ነው። ልክ ነው? እውነት ከሆነ፡ ጉባኤ ውስጥ ያለ ሰው እንዲያይሽ እጅሽን አንሺ። አሁን፡ እዚህ የቆመች ሴት ብቻ ናት።

131 ተመልከቱ፡ እስቲ ወደ ቅዱሳት መጻሕፍት እንመለስ። ቅዱስ ዮሐንስ 4ን እንውሰድ። እያንዳንዳችሁ ወደ ቤት ስትሄዱ አንብቡት። ይህች ሴት የዚያ ዓይነት ሴት ናት ማለት አ—አይደለም፣ አላውቅም። እኔ ኢየሱስ ክርስቶስ እንዳልሆንኩ ታውቃላችሁ። ነገር ግን እርሱ እዚህ አለ። እርሱ ነው። አሁን መንፈሱ እኛን እየቀባን ነው፡ ልክ ለሴቲቱ ጉድጓድ ላይ እንዳደረገው፡ የእሷን ችግር ሊገልጥላት ይችላል። ተመሳሳይ ነገር።

132 የዚያን ጊዜ፡ ካህናትና፡ መሪዎች፡ እንዲህ አሉ፡ "ይህ ሰው ሟርተኛ ነው፡ ወይም ዲያብሎስ፡ ቤልዜቡል ነው" አሉ።

133 በዚህ ጊዜ ሴትየዋ፡ "ጌታዬ፡ አንተ ነቢይ እንደሆንክ አስተዋልኩ። መሢሕ እንደሚመጣ እናውቃለን፡ ይህም ምልክት ይሆናል።"

134 አሁን፡ ይህ እውነት መሆኑን ስንቶቻችሁ ታውቃላችሁ? ደህና፡ ትላንትናም፡ ዛሬና፡ ለዘለዓለም ያው ከሆነ፡ ዛሬ ማታ ይህ የእርሱ ምልክት አይሆንም? ከዘመን መጨረሻ በፊት፡ እንደሚሆን ቃል ገብቶልን ነበርን? አሁን ለአብርሃምን ዘር የገባውን ቃል እንደሚጠብቅ እንመልከት።

135 አሁን እዚህ ውስጥ ያለ ማንኛውም ሰው ይህ ስሕተት ነው ብሎ የሚያስብ ከሆነ፡ ወደዚህ ይምጣና ተመሳሳይ ነገር ያድርጉ። ካልሆነ፡ ስለዚህ ጉዳይ ምንም ነገር አይናገር። መብት አላችሁ።

136 አሁን፡ በክርስቶስ ስም፡ ለእግዚአብሔር ክብር፡ እያንዳንዱን መንፈስ በቁጥጥሬ ሥር አደርጋለሁ።

137 ከአንቺ ጋር፡ ትንሽ መነጋገር አለብኝ፡ አንቺ ወጣት እመቤት። ታውቂያለሽ፡ ጌታችን ጉድጓድ አጠገብ ከዚያች ሴት ጋር ሲነጋገር ነበር። እሱም እንዲህ አላት፡ "ውሃ አምጭልኝ።" ምን እያደረገ ነበር?

138 አሁን ተመልከቱ፡ በቅዱስ ዮሐንስ 5 ላይ፡ እንዲህ ብሏል፡ "እውነት፡ እውነት፡ እላችኋለሁ፡ ወልድ፡" እርሱ ነበር፡ በአካል፡ አብ ሲያደርግ ያየውን ካልሆነ በቀር፡ "ወልድ ከራሱ ምንም ሊያደርግ አይችልም።" "አብ የሚያደርገውን፡ ለልጅ ያሳየዋል። አያችሁ፡ ከራሴ ምንም ማድረግ አልችልም፡ ነገር ግን አብ ሲያደርግ እንዳየሁት አደርገዋለሁ።" ከዚያም፡ አስቀድሞ እግዚአብሔር በራዕይ ካላሳየው በቀር፡ ኢየሱስ አንድም ተአምር አላደረገም። በጆሮው ነገርው ሳይሆን፡ በራእይ አሳየው። "የማየውን፡" የሚሰማውን አይደለም፡ "አብ ሲሰራ ያየሁትን።" ሙሴ እንደተናገረው፡ እንደ ሙሴ ነቢይ ያደረገው ያ ነው። አሁን እርሱ አ—አብን ሲያውቅ... እሱ...

139 ኢየሱስ ወደ ኢያሪኮ እየተጓዘ ሳለ፡ በሰማርያ በኩል ማለፍ ነበረበትና፡ ወደ ሲካር ከተማ ደረሰ። አሁንም አያችሁ፡ ሳምራውያን መሲሕ ይጠብቁ ነበር።

140 አይሁድም ይፈልጉት ነበር፡ ምልክቱንም አሳያቸው። ፊልጶስ፡ ናትናኤል፡ ጴጥሮስ፡ ይህ ምልክት እንደተፈጸመ ወዲያውኑ፡ እንዲህ አሉ፡ "አንተ የእግዚአብሔር ልጅ ነህ።"

ራባዩም፡ "ይህ ሰው ቤልዜቡል ነው" አለ።

141 አሁን ግን አስታውሱ፡ እኛ አሕዛብ፡ እኛ፡ አንግሎ-ሳክሰን ነበርን፡ ም—ምንም መሢሕ እየተጠባበቅን አልነበረም። እኛ አረማውያን፡ ሮማውያንና ወዘተ ነበርን። የመሲሑን መምጣት አልጠበቅንም። እርሱ የሚመጣው ለሚፈልጉት ብቻ ነው።

142 ነገር ግን ሳምራውያን እየፈለጉት ስለነበር፡ በሰማርያ በኩል፡ ማለፍ ነበረበት። በጉድጓዱ አጠገብ ተቀመጠ። አንዲት ወጣት፡ ምናልባትም ያንቺ እድሜ ክልል የሆነች ሴት፡ ወጣች። ሲቲቱም ክፉ-ስም የነበራት ሴት ነበረች። ታሪኩን አንብበሻል ብዬ፡ እገምታለሁ። እርሱም፡ "አንቺ ሴት፡ ውኃ አምጪልኝ" አላት።

143 "ኡህ፡ አንተ አይሁዳዊ ሆነህ፡ ሳምራዊን፡ እንዲህ ያለ ነገር መጠየቅ የለብህም፡" አለችው።

144 ኢየሱስም፡ "ማንን እንደምታነጋግሪ ብታውቂ፡ እኔን መጠጥ እንድሰጥሽ ትጠይቂኝ ነበር" አላት።

145 ንግግሩ ቀጠለ። በመጨረሻም፡ ችግሯን አገኘ። ምን እንደነበረ ታስታውሺያለሽ? በጣም ብዙ ባሎች ነበሯት። እንዲህ አላት፡ "ሂጂ ባልሽን ጥሪና፡ ወደዚህ ነይ" አላት።

እሷም፡ "ምንም ባል የለኝም" አለች።

146 እንዲህ አላት፡ “ልክ ብለሻል፡” አላትም፡ “ምክንያቱም አምስት ባሎች አሉሽ፡ አሁን አብረሽ የምትኖሪው ባልሽ አይደለም” አላት።

147 እሷም፡ “ጌታ ሆይ፡ አንተ ነቢይ እንደሆንክ አያለው። መሢሑ ሲመጣ እነዚህን ነገሮች እንደሚነግረን፡ እናውቃለን” አለችው።

እርሱም፡ “እኔ እሱ ነኝ” አላት።

148 እርሷም የውኃ ማሰሮዋን ትታ፡ ወደ ከተማዋ እየሮጠች ሄደች፡ እንዲህም አለች፡ “ኑና፡ ያደረግሁትን ሁሉ የነገረኝን ሰው እዩ። ይህ ክርስቶስ አይደለምን? ” በመቶዎች ለሚቈጠሩ ዓመታት ነቢይ አልነበራቸውም። እነሆ መሢሕ ነኝ የሚል ሰው ነበር፡ ነቢይ መሆኑን እ—አረጋግጧል፡ የመሲሑን ምልክት አሳይቷል።

149 እሱ እርሱ ትናንትና፡ ዛሬና ለዘላለም ያው እንደመሆኑ፡ እንደሚያደርገው፡ በእነዚህ ቅዱሳት መጻሕፍት ቃል እንደገባ፡ ተመሳሳይ ነገር ቢያደርግ፡ ተመሳሳይ ነገር እንድታምኚ ያደርግሻል?

ጉባኤውን እንዲያምኑ ያደርጋቸዋልን?

150 የኩላሊት ችግር አለብሽ። ያ ትክክል ከሆነ፡ እጅሽን አንሺ።

151 ይህ ሁልጊዜ ፊቴ ላይ የሚያንዣብበው ለምንድን ነው? አንድ ሰው እንዲህ ይላል፡ “ገምቶ ነው።” መቼም ገምቼ አላውቅም።

152 እነሆ፡ ቈንጆ ሴት ነች። ታምኚያለሽ? እንዳልገመትኩት ታውቂያለሽ። ሌላ ነገር ልንገርሽ። ባለቤትሽ ከአንቺ ጋር ነው። እሱም፡ እየተሰቃየ ነው። አይደል? የአከርካሪ አጥንት ሕመም። ልክ ነው። አይደል? ከእናንተ ጋር አንድ ትንሽ ልጅ ይዛችኋል። እሱም፡ እየተሰቃየ ነው። እንዲፀለይለት ትፈልጊያለሽ። በዓይኖቹ የሆነ ችግር አለው። በትክክል። ካንቺ ጋር አንዲት ትንሽ ልጅ አለች፡ እሷም እንደ አንቺ፡ የኩላሊት ችግር አለባት። ልክ ነው? አሁን ሁላችሁም ጤነኛ ልትሆኑ ትችላላችሁ፡ የምታምኑ ከሆነ። ታምኚያለሽ? እግዚአብሔር ይባርክሽ። ሂጂ ሰላምም ሁኚ።

153 ታምኚአለሽ? እሱ ትናንት፡ ዛሬና፡ ለዘላለም ያው እንደሆነ። ምን ማለት ነው? ምን ለማድረግ እየሞከረ ነው? ለአንቺ፡ ለአብርሃም ዘር፡ የሞተ አለመሆኑን ያሳያል። እኔ እነዚህን ነገሮች ማድረግ አልችልም። እርሱ አልሞተም። ነገር ግን ሕያው ነው፡ የጠላትን ደጅ የመውረስ ስልጣን እንዳላችሁ እያሳየ ይገኛል። ይህ ይበቃል በቃ።

154 ይህች እመቤት፡ እስቲ ለአፍታ፡ ወደዚህ ነይ። በተመሳሳይ፡ ዕድሜ ላይ እንገኛለን፡ ብዬ እገምታለሁ። ነገር ግን እ—እስከማውቀው ድረስ፡ አንዳችን ለሌላው እንግዶች ነን። አላውቃትም፡ እንግዶች ነንና። ስለ አንቺ ምንም አላውቅም። ያ ትክክል ከሆነ፡ እጅሽን አንሺ፡ አየሽ። [እህት፡ “ልክ ነው” አለች።—እርታዒ።] ከእነርሱ አንድ ሰው የጸሎት ካርድ ሰጦሻል፡ አንቺም እዚህ ነሽ። መልካም። አሁን ጌታ ኢየሱስ...

155 ምናልባትም፡ የወንድም ኦራል ሮበርትስን ቦታ ለመውሰድ እየሞከርኩ፡ ከሆነ፡ ወይም የእነዚያ ታላላቅ የእምነት ሰዎች ቦታ ለመውሰድ እየሞከርኩ ከሆነ፡ እንዲህ እላለሁ፡ “እመቤት፡ ችግርሽ ምንድነው? ”

156 እንቺም፡ “አዎን፡ እኔ **እንዲህ-እና-እንዲያ** አለብኝ” ትያለሽ። አሁን፡ እሱ ትክክል ላይሆን ይችላል። አየሽ? አላውቅም። አየሽ? ነገር ግን፡ ለእርሱ፡ ምን ችግር እንዳለብሽ ልትነግረው ትችያለሽ።

157 እጆቹን በላይሽ ላይ ጭኖ፡ እንዲህ ይላል፡ “እግዚአብሔር ለ—ለታመሙ ሰዎች እንድጸልይ ልኮኛል። ይህን ታምኚያለሽ? ” “አዎን።” “ክብር ለእግዚአብሔር! ሂጂ፡ እመኚ።”

158 መልካም። መልካም። እግዚአብሔር ቃል ገብቶልናል። ነገር ግን፡ እኛ፡ ከዚህ ቀን ትንሽ ራቅ ብለን እ—እየኖርን ነው። ኢየሱስ ቃል ገብቶልናል፡ “በሰዶም ዘመን እንደነበረ ነው። እኔ የማደርገውን ሥራ እናንተም ደግሞ ታደርጋላችሁ።”

159 አሁን፡ እግዚአብሔር ምን እንደሆንሽ ሊነግረኝ ከቻለ፡ እውነትም ይሁን አይሁን ታውቂያለሽ፡ ምን እንደምትሆኚ ሊነግርሽ ይችላል፡ ያ እውነት ከሆነ፡ ይህም፡ እውነት ይሆናል።

160 እርሱ ቢነግርሽ፡ ምንም ይሁን ምን፡ እኔ አላውቅም፡ ነገር ግን እሱ ችግርሽ ምን እንደሆነ ከነገረኝ፡ እናንተም፡ ጉባኤዎችም፡ ታምናላችሁ?

161 ይህን ነገር በእውነት ማቆም አለብኝ። አሁን አንድ ጊዜ፡ አሁን የመጣችው ሴት፡ ያ ማረጋገጥ አለበት። ኢየሱስ አንድ ጊዜ ነው ያደረገው። እንደገና አላደረገም። በሲካር ውስጥ የሚኖር ሰው ሁሉ አመነ፡ የሴቲቱን ምስክርነት አመነ፡ ስትመጣ፡ ነገረቻቸው፡ እሷ መጥፎ-ስም ያላት ሴት ነበረች። አንድ ክርስቲያን በሁላችሁም ፊት፡ አሁን ከመድረክ ወርዷል! አሜን። ነገር ግን እኛ ከምናስበው በላይ ዘግይቷል፡ ጌታ እራሱን ማረጋገጡን ይቀጥል፡ ታላቁ ኃያል አሸናፊ፡ የአብርሃም ዘር... ነገር ግን እንደ አብርሃም፡ በአንድ ወቅት፡ በአብርሃም ዘንድ አደረገው፡ ከዚያም ያንን አጠፋው፡ እንደገና አደረገው። አብርሃም ያለማቋረጥ እግዚአብሔርን ያምን ዘንድ።

162 እዚህ የመጣሽው ለራስሽ አይደለም። እዚህ የመጣሽው ስለ ሌላ ሰው ነው፡ ሴት ናት። እህትሽ ናት። ሴቲቱም በሞት አፋፍ ላይ ነች። በ—በስኳር ሕመም እየተሰቃየች ትገኛለች። ከዚህ አይደለችም። ከ... ከሉዊዚያና ነው የመጣችው፡ ከጭቃማ ከሆነች አገር። ያ... ይሄው ሌላ ነገር፡ ጉባኤ ይህን ያውቁ ይሆናል። በጣም የታመመች ሴት ልጅ አለችሽ፡ በዚህ ስብሰባ ላይ ለመገኘት እያሰበች ነው፡ የሚጥል በሽታ አለባት። ይህ እውነት ነው። ይህ እውነት ነው። አይደል? አሁን ታምኚያለሽ? [እህት፡ “አዎን። አሜን” አለች።—አርታዒ።] የአብርሃም ዘር ከሆናችሁ፡ ተቀበይና ውጪ፡ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ተፈወሺ።

163 ታምኚያለሽ? በእርግጠኝነት። አስታውሱ፡ የሱ ቃል ኪዳን ነው። አደርገዋለሁ ብሏል። የገባውን ቃል ይጠብቃል።

164 እንዴት ነሽ? እርስ በርሳችን እንግዶች ነን። እኔ አላውቅሽም። ነገር ግን እግዚአብሔር ያውቅሻል። እግዚአብሔር ችግርሽን ሊገልጥልኝ እንደምችል ታምኚያለሽ፡ ከሆነ ከመንፈሳዊ ኃይል መምጣት እንዳለበት ታውቂያለሽ። አሁን፡ ሊመጣ የሚችለው ከሁለት ነገሮች ብቻ ነው፡ መገመት ትችላላችሁ። ሲከናወን፡ ከማብራራት በላይ ነው፡ ምክንያቱም ክስተት ነው። እናም፡ ደግሞም፡ እያዎ ነው፣ ብቻ፡ የሆነ፡ ምክንያታዊ ያልሆነ፡ ነገር ግን እውነት የሆነ ነገር ነው። ይህም እያዎ

ይባላል። አሁን እውነትም ይሁን አይሁን፡ ታውቂያለሽ፡ የነገረሽ ነገር እውነቱን መሆኑን ታውቂያለሽ።

165 አሁን፡ አስታውሺ፡ እኔ አላውቅሽም። ከጀርባዬ የሆነ ሰው መኖር አለበት። እንደ ፈሪሳውያን ካደረጋችሁ፡ እንዲህ፡ "ኦህ፡ ክፉ መንፈስ ነው" ካላችሁ፡ የዛን ሽልማት ትቀበላላችሁ። ይህ ክርስቶስ ነው ብላችሁ ካመናችሁ፡ ሽልማቱን ታገኛላችሁ። ይህን ማመን የምትችሉበት ምክንያት፡ እርሱ ለዚህ ዘመን ቃል ስለገባ ነው፡ ከዚያን ጊዜ አንሥቶ እስከ ዛሬ ድረስ ግን አልሆነም። ይህም የመጨረሻውን ዘመን ያደርገዋል።

166 አንድ ሰው ያለማቋረጥ፡ በፊትሽ ይታያል። ወንድ ነው፡ ግራጫ-ጸጉር ያለው። ባልሽ ነው። እዚያ ተቀምጧል። በካንሰር፡ በእብጠት፡ በካንሰር ጥላ ስር ሆኖ፡ ፈውሱን ለመቀበል እየሞከረ ነው፡ አንቺም የኩላሊት ችግር፡ የፊኛ ችግር አለብሽ። አቶ እና ወይዘሮ ሊትል ትባላላችሁ። ልክ ነው? [ሴቲቱም "አዎን፡" አለች።—አርታዒ።] በሙሉ ልባችሁ እመኑና፡ ተፈወሱ።

167 "ስማቸውን፡ ትናገራለህን? " እንዴታ፡ በደንብ። ኢየሱስ ጴጥሮስን፡ "ስምህ የዮና ልጅ፡ ስምዖን ነው" አላለውምን?

168 እነሆ አንድ ሰው እዚህ ነው። እርሰ በርሳችን እንግዳ ነን፡ ወዳጄ። አላውቅህም። ነገር ግን አንተ፡ ልክ እ—እንደ ጴጥሮስ ወደ ጌታ ኢየሱስ ሲመጣ እንደነበረው ነህ፡ በእምነት አንድ ነን። የእርሱ አገልጋይ እንደሆንኩ ታምናለህ? የተናገርኩት ነገር እውነት ነው ብለህ ታምናለህ? [ወንድም እንዲህ አለ፡ "አዎን፡ ወዳጄ። አምናለሁ፡ ወዳጄ፡"—አርታዒ።] ማመን ከቻልክ! እኔ፡ ላደርግልህ የምችለው ነገር ቢኖር፡ አደርገው ነበር፡ ነገር ግን ምንም ማድረግ የምችለው ነገር የለም። አስቀድሞ አድርጓታል፣ እንድታምን የሚያደርገው ያ ነው። እናም፡ አየህ፡ እኔ አይደለሁም። እኔ ብሆን ኖሮ፡ የ—የምችለውን ሁሉ አደርግልሃለሁ። እርሱ ግን ስጦታ ሰጠኝ፡ እኔ ራሴን በፊቱ አሳልፌ እሰጣለሁ፡ እሱ እኔን ተጠቅሞ ይናገራል። ይህን ታምናለህ? ["አዎን።"]

169 ጉባኤስ፡ ይህን ታምናላችሁ?

170 ትክክለኛ ሰው ፈልጌ ነበር። ብዙ ችግሮች አሉብህ። ነገር ግን አንዱ ነገር፡ በቀኝ ዓይንህ ላይ እብጠት አለብህ። ያ ዋናው ችግርህ ነው። ይሄው ሌላ ነገር፡ አንዲት ሴት እዚህ ብቅ ትላለች። ሚስትህ ነች። በሚስትህ ላይ ያለውን ችግር እግዚአብሔር ሊነግረኝ እንደሚችል ታምናለህ? ችግሯ በአፍዋ ላይ ነው። ጥርሶቿ ናቸው። በትክክል። ያንኑ ኢየሱስ ታምነዋለህን፡ ስምዖን ጴጥሮስ ማን እንደሆነ ያወቀው፡ አንተ ማን እንደ ሆንክ ሊነግረኝ እንደሚችል ታምናለህን? [ሰውዬው "አዎን፡" አለ።—አርታዒ።] በጣም እንድታምን ያደርግሃልን? ["አዎን፡ ወዳጄ።"] ያደርጋል? ["አዎን።"] ኦስካር ባርነስ። ["ትክክል ነው።"] ልክ ነው? ወደ ቤትህ ሂድ፡ ተፈወስ።

171 [በቴፕ ላይ ባዶ ቦታ አለ—አርታዒ።]... ላንተ እንግዳ ነኝ። እኔ አላውቅህም፡ እግዚአብሔር ግን ያውቅሃል። ችግርህ ምን እንደሆነ ሊነግረኝ እንደሚችል ታምናለህ? በሙሉ ልብህ ታምናለህ? ችግርህ በጉሮሮ አካባቢ ነው፡ እዚህ ደረትህ ጋር ነው። የ—የአጥንት መበስበስ ነው። በአጥንትህ ውስጥ፡ ልክ እንደ እብጠት ያለ ነገር፡ እንጓ መሳይ ነገር አለብህ። በትክክል። ከዚህ አይደለህም። የመጣኸው በ—በዙሪያዋ የብርቱካን ዛፎች ካላት ከተማ

ነው። ከበስተጀርባው የተራሮች ፓኖራሚክ ባለባት፡ ሸለቆ ያለች ስፍራ። በዚያም አንትለርስ የሚባል ሆቴል አለ። ሳን በርናርዲኖ ናት። የመጣኸው ከዛ ነው። ተመለስ፡ ካመንክ፡ ኢየሱስ ክርስቶስ ደህና ያደርግሃል።

172 ካንሰርን የሚፈውስ አንድ ነገር ብቻ ነው፡ እሱም እግዚአብሔር ነው። እንደሚፈውስህ ታምናለህ? [ያ ወንድም፡ "በእርግጠኝነት አምናለሁ፡" አለ።—አርታዒ።] እመን! ሂድ፡ ጌታ አምላክ ሁለመናህን ይፈውሰው።

173 ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በጣም ተ-... ተጨንቀሃል፡ በጣም ተበሳጭተሃል። በዚህ የመረበሽ ስሜት፡ ሆድህን አሞሃል። ምግብህን መፍጨት አልቻልክም፡ ያስመልስሃል። በአፍህ ውስጥ ያለው ሙሉ አሲድ ነው። ከሰዓት በኋላ፡ እውነተኛ ድካምና ብዙ ነገር ይሰማሃል። በሆድህ ውስጥ የፔፕቲክ ቁስለት አለብህ። ኢየሱስ ክርስቶስ ይህን ሊነግርሽ እንደሚችል ታምኛያለሽ? [ያች እህት "አዎን፡" አለች።—አርታዒ።] እንደዚያ ከሆነ፡ ሂጂ እራትሽን ብይ። በፍጹም ልብሽ እመኚ፡ ኢየሱስ ክርስቶስ ይፈውስሻል።

174 እንዴት ነሽ? ብዙ ችግር አለብሽ። ነገር ግን ከምትፈሪያቸው ነገሮች መካከል አንደኛው፡ በአርትራይተስ ምክንያት ሽባ መሆን ነው። ነገር ግን እግዚአብሔር እንደሚፈውስሽ፡ ታምኛያለሽ? [እህት እንዲህ አለች፡ "አዎ።"—አርታዒ።]

175 ጌታ ኢየሱስ ሆይ፡ ለእህቴ ፈውሱን እንድትሰጣት እጸልያለሁ። ማየት እንድትችል አድርጋት። የሴቲቱን ችግር ከላዩዋ ውሰድላት፡ የሷን አርትራይተስን ፈውስ፡ በኢየሱስ ስም። አሜን።

176 እያመንሽ፡ ሂጂ። ያደርገዋል፡ ደህና ትሆኚያለሽ። አትጠራጠሪ፡ መሄዱን ቀጥይ፡ በሙሉ ልብሽ እመኚ።

177 የልብ ችግር በጣም ከባድ ነገር ነው፡ ነገር ግን ክርስቶስ ልብን ይፈውሳል። ይህን ታምኛያለሽ? [እህት፡ "አዎ" አለች።—አርታዒ።] ሂጂ፡ እመኚ፡ ሁሉም ነገር ያበቃል። አበቃ።

178 ሽባ እሆናለሁ ብለሽ ታምኚያለሽ? አይ፡ እኔም፡ አላስብም። ሃሳቤ፡ አርትራይተስ፣ እዚያ ያለው ጥላ፡ ኦህ፡ ያ ካንሰር ነው። እንደሚፈውስሽ ታምኛያለሽ? [እህት፡ "አዎ፡ አምናለሁ።"—አርታዒ።] ሂጂ፡ እመኚ። ሙሉ ያደርግሻል።

179 ለረጅም ጊዜ ሲያስቸግርሽ ቆይቷል፡ በልብሽ ውስጥ ያፍንሻል። ነገር ግን ዛሬ ማታ ያበቃል ብለሽ ታምኚያለሽ? ሂጂ፡ እመኚ፡ ኢየሱስ ክርስቶስ ይፈውስሻል።

180 ለረጅም ጊዜ፡ የሴቶች ወግ ችግር፡ ሲያስጨንቅሽ ቆይቷል። ከዚያም፡ አንቺ፡ በማለዳ ለመነሳት ትቸገሪያለሽ። እጅና እግርሽ፡ ይደነዝዛሉ። በቀኑ፡ እስከረፋድ ድረስ፡ መራመድ አትችይም። አርትራይተስ ነው። ሂጂ፡ አትጠራጠሪ፡ ከእንግዲህ አይኖርብሽም። በሙሉ ልብሽ፡ እመኚ።

181 ብዙ ውስብስብ፡ ነገሮች አሉብሽ። በጣም የሚረብሽሽ ነገር ግን፡ የአርትራይተስ በሽታ ነው፡ እሱም፡ ሽባ እያረገሽ ነው። እንድትራመጂና ደህና እንድትሆኚ እንደሚያደርግሽ ታምኚያለሽ? [ያች እህት፡ "አዎን፡

ጌታዬ" አለች።—አርታዒ።] ሂጂ፡ በፍጹም ልብሽ እመኚ፡ ኢየሱስ ክርስቶስ ይፈውስሻል።

182 የልብ መጣበብ፡ የአርትራይተስ በሽታ ያለብሽ ቢሆንም፡ ነገር ግን እንደሚፈውስሽ ታምኚያለሽ? አምነሻል ወይ? ሂጂ፡ ጌታ ኢየሱስ ይፈውስሽ።

183 ያ የሆድ ህመም ባለፉት ጥቂት አመታት ውስጥ ብዙ አሞሻል፡ አይደል? ከዚህ በኋላ አያምሽም። ሂጂ፡ እመኚ። እግዚአብሔር ይባርክሽ። ተፈወሺ።

184 እንዲሁም፡ ሆድሽ፡ ተፈውሷል። ሂጂ፡ በፍጹም ልብሽ እመኚ። አትጠራጠሪ።

185 ለመተንፈስ ተቸግረሃል፡ በእርግጥ አስም የሚባል በሽታ አሞሃል፡ አይደለም እንዴ? አሁን ያ በሽታ ያበቃል ብለህ ታምናለህ? [ወንድም እንዲህ አለ፡ "አዎ።"—አርታዒ።] እሺ፡ ሂድ እመን። አሜን።

186 ሃሌ ሉያ! በሙሉ ልብህ ታምናለህን?

187 ለአንድ አፍታ። ያንን ብርሃን እዚያ ታየዋለህን? አንዲት ትንሽ ጠቆር ያለች ሴት እያየችኝ ነው፡ እዚህ ተቀምጣለች፡ በግራ ጎኗ ውስጥ እብጠት አላት። የኩላሊት ችግር አለባት፡ ውስብስብ ችግሮች አለባት። የሚበልጥ እምነት አለሽ። እዚህ መምጣት አይጠበቀብሽም። አበቃ። እመኚ። አሜን። በእግዚአብሔር እምነት ይኑርሽ!

ይህን ታምኚአለሽን?

188 ታምኚያለሽ፡ እህቴ፡ በተቀመጥሽበት፡ ያንን የአከርካሪ አጥንት ችግር እንደሚለቅሽ? እንደሚፈውስሽ ታምኛለሽ? እሺ። አትጠራጠሪ፡ ካመንሽ እንደእምነትሽ ይሁንልሻል።

189 እዚህ የተቀመጠው ሰው፡ እኔን እያየኝ ያለው፡ በፕሮስቴት በሽታ ይሰቃያል፡ በሌሊት መነሳትና ሌሎች ነገሮችን ማድረግ። ታምናለህ፡ ወዳጄ? ካመንክ፡ ከዚያም፡ ያበቃል።

190 እዚህ አንድ ጥቁር ሰው ተቀምጧል፡ እኔን እያየኝ ነው። በሚጥል በሽታ እየተሰቃየ ነው። የመንፈስ ቅዱስን ጥምቀትም ይፈልጋል። በእግርህ ቁም፡ ወዳጄ፡ ፈውስህን ተቀበል። እግዚአብሔር የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀትን ይስጥህ። ኣሜን።

191 ከፊት ለፊትህ፡ የተቀመጠ ልጅ አለ፡ ኤፒሌፕሲ አሞታል፡ ራሱን እየሳተ ይወድቃል፡ በሌላኛው ጎን፡ እዚያ ተቀምጧል። እግዚአብሔር እዚያ ልጁን ደህና ያደርገዋል፡ ብለህ ታምናለህ? በሙሉ ልብህ ታምናለህ? ከዚያም እግዚአብሔር ሕፃኑን ይፈውሳል።

192 እያንዳንዳችሁ፡ ታምናላችሁ? በ—በ—በእውነት የአብርሃም ዘር አይደለምን? እርሱ ኃያሉ አሸናፊ አይደለምን? የጠላትን ደጆች እንደምትወርስ ቃል ገብቷል?

193 ስንቶቻችሁ ታስራችኋል፡ የጠላት ግፊት ይሰማችኋል? የጠላት ግፊት የሚሰማችሁ፡ እጆቻችሁን አንሱ፡ የአብርሃም ዘሮች ናችሁ፡ **እንደዚህ** እጆቻችሁን አንሡ። እንዲህ በሉ፡ "ወንድም ብራንሃም፡ በጭንቀት ተጨንቄያለሁ።" ኡህ፡ ሰማንያ በመቶ ይምታክሉ እንደዛ ናችሁ። አሁን፡ በ... በጣም ወፍራም እየሆነ

ነው፡ መላው ሕዝብ እንደ ትልቅ የጭጋግ ብዥታ ይመስላል፡ ያላችሁበት ቦታ ሁሉ፡ ማየት እያቃተኝ ነው።

194 በዚህ መድረክ ላይና፡ በዚያ ጉባኤ መካከል፡ እዚህ ሀያ፡ ወይም ሠላሳ፡ ወይም ከዚያ በላይ፡ የሆኑ ጉዳዮችን በሙሉ፡ እግዚአብሔር እንደማይሳሳት አታዩም? ኢየሱስ ክርስቶስ ትናንት፡ ዛሬ፡ ለዘላለም ያው ነው እርሱ ነው። ይህን ታምናላችሁ? [ጉባኤው፡ “አሜን” አለ።—አርታዒ።] ታዲያ ለምንድነው፡ የአብርሃም ዘር የሆናችሁ ሁሉ፡ ለምን አሁን ቁልፋን አትወስዱትም? ታላቁ ድል አድራጊ፡ ለናንተ ያሸነፈው፡ እዚህ ይገኛል። እዚህ መገኘቱን አረጋግጧል። በእርሱ ታምናላችሁን?

195 ከዚያም የእምነት ቁልፋችሁን ወሰዳችሁ፡ እጃችችሁን ወደ ላይ ዘርግታችሁ፡ እንዲህ በሉ፡ “ኢየሱስ ክርስቶስ፡ አሁን፡ ለመፈወሴ እምናለሁ” በሉ። በእግሮቻችሁ ቁሙ። እጃችችሁን አንሡ፡ ዕምነታችሁን አሁን አስሩት። “ጌታ ኢየሱስ፡ አምንሃለሁ። አሁን አምንሃለሁ።”

196 አሁን እጃችችሁን እርስ በእርሳችሁ ላይ አድርጉ። እጃችችሁን እርስ በእርሳችሁ፡ በሌላ አብርሃም ዘር ላይ አድርጉ። አሁን ስለዚያ ሰው ትጸልያላችሁ። እጃችችሁን ጫኑባቸው። ኢየሱስ እንዲህ ብሎል፡ “ያመኑትን እነዚህ ምልክቶች ይከተሉአቸዋል። እጃቸውን በድውዮች ላይ ቢጭኑ፡ ይድናሉ።”

197 ሰይጣን ሆይ፡ ጦርነቱን ተሸንፈሃል። በኢየሱስ ክርስቶስ ስም፡ ከዚህ ውጣ፡ ስለ እግዚአብሔር ክብር፡ ይህን ሕዝብ ልቀቅ።

64-0207 የአባቶች አለቃ አብርሃም
ከርን ካውንቲ ፌርግራውንድስ
ቤከርስፊልድ, ካሊፎርኒያ ዩ.ኤስ.ኤ

AMHARIC

©2025 VGR, ALL RIGHTS RESERVED

VOICE OF GOD RECORDINGS
P.O. BOX 950, JEFFERSONVILLE, INDIANA 47131 U.S.A.
www.branham.org

## የቅጂ መብት ማሳሰቢያ

ይህ መጽሐፍ የኢየሱስ ክርስቶስን ወንጌል ይሰፋ ዘንድ፣ በቤት ለግል ጠቀሜታም ሆነ ለሌሎች ሰዎች ያለ ክፍያ ለማበርከት፣ በቤት ማተሚያን መጠቀም ይቻላል። ይህ መጽሐፍ ያለ ቮይስ ኦፍ ጋድ ሪከርዲንግስ በጽሑፍ የተደገፈ ህጋዊ ፈቃድ መሸጥም ሆነ፣ አብዝቶ ማተም፣ በዌብ ሳይት ላይ ማስቀመጥ፣ በማከማቻ ዘዴዎች ላይ ማስቀመጥ፣ ወደ ሌሎች ቋንቋዎች መተርጎምም ሆነ የድጋፍ ማሰባሰቢያ አድርጎ መጠቀም የተከለከለ ነው። ህጋዊ መብቱም ሁሉ የተጠበቀ ነው®።

ለተጨማሪ መረጃ ወይም ተጨማሪ ግብዓቶች ቢፈልጉ፣ እባኮትን ይህ አድራሻ ይጠቀሙ፡

VOICE OF GOD RECORDINGS
P.O. BOX 950, JEFFERSONVILLE, INDIANA 47131 U.S.A.
www.branham.org